"እንደዚያ ይመስለኛል" ሲሉ መለሱለት::

"የተያዘው የፀጥታው ኃላፊ ከወሮበላዎቹ ጋር ግንኙነት ስለነበረ መንገድ የሚከፍት ይመስለኛል::"

"ምርመራውን ጠበቅ አድርገው ከያዙት እንዳልከው አንድ ፍን መገኘቱ የማይቀር ነው:: ለማንኛውም የእኛን ሰው ደውለህ ትጠራል እንድንገናኝ ታደርግልኛለህ:: በዚህ ዙሪያ በደንብ መነጋገር አለብኝ" አሉት::

"ደውዬለት ነበር" አለ ጸሐፊያቸው::

"እንዴት ለምን ጉዳይ ነበር የደወልክለት?" አሉ ግር ብሏቸው::

"ደውልና አገናኘኝ ብለው ነበር እኮ እረሱት እንዴ?" አለ ጸሐፊያቸው:

የመምሪያው ኃላፊ ሃፍረት ቢጤ የተሰማቸው መሰሉ::

"ይቅርታ ረስቼው ነው:: ሪፖርትም ደርሶኛል:: ለማንኛውም ደግመ ደውልለት:: ነገሩ ወደ ጫፍ እየደረሰ ስለ ሆነ በትኩረት መከታተ ይኖርብናል:: ጡዘቱ ሲፈጥን እኛም መፍጠን አለብን" አሉት::

"ከሰዓት እንደሚመጣ ነው ቀጠሮ የሰጠኝ ሁሉንም ነገር በቅር ይከታተለዋል የሚል እምነት አለኝ" አለ ጸሐፊው::

"የደኅንነት መዋቅሩ አሠራር የተጠናከረ ይመስላል::"

"ትክክል ነዎት በጣም የተሻለ ለውጥ እየመጣ ነው:: ብዙ ነገሮ እየፈለፈለ በማውጣት ላይ ነው ያለው::"

"በዚህ ከቀጠሉ በቅርብ ቀን የነገሩ አስኳል ይገኛል የሚል እምነ አለኝ:: ከሚደርሰን መረጃ እንደ ተረዳሁት የሁሉም ነገር ጫፍ እየተገ ነው:: እንቅልፍ የለም በርትታችሁ ተከታተሉ" ሲጋራ ፍለጋ ወደ ኪሳቸ ገቡ::

"አደጋ ላይ ተኝተን እንዴት ነው የምናቀላፋው?" አለ ጸሐፊው::

"በየደቂቃው የሚመጡትን መረጃዎች እየተቀበልክ አድርስ:: ማንም ሰው መተኛት የለበትም:: የአበሾቹ የጸጥታ መሥሪያ ቤት በጣም እየፈጠ ስለሆነ እኛም ጡዘቱን ተከትለን መሽከርከር ይኖርብናል:: በጣም ፍጠኑ" ሲጋራ ሲያቀጣጥሉ እንዳሰናበቱት ገባውና ከተቀመጠበት ተነሳ ረዳታቸው::





# ምእራፍ ሃያ አምስት

"ዓለም ምን እንደሚል ሳስብ ይገርመኛል" አለ ኢንጂነሩ ራሱን እያሻሸ::

"ምንም የሚያስገርም ነገር አይኖርም:: አሁን የምንመለከተው የሰው ዘር ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት ከሌሎች ፍጡራን መዳቀል የተገኘ ነው ተብሎ ይታመናል:: ዘመኑ እየራቀ ሲመጣ ሁሉም ነገር ወደ ተረት እየተቀየረ ነበር፣ አሉ እየተባለ ይተረክለታል:: ለምሳሌ በቻይና ግዛት በአንድ ወቅት የተገኙት ሰው መሰል ፍጡራን በአንድ ወቅት ከዮፎዎች የተዳቀሉ የሰው ልጅ ዝርያ እንደ ሆኑ ይገመታል::"

"በቻይና ተገኙ የተባሉት የሰው ዝርያዎች አሁን ካለው የሰው ልጅ ዝርያ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ሊያስረዱን የሚችሉ ምንም የሥነ-ፍጥረት መረጃዎች የሉም::" አለ ኢንጂነሩ::

"የሚመሳሰሉበትም የሚለያዩበትም መንገድ ስላለ ከሚመሳሰሉበት ብንነሳ በ 1960ዎቹ መጀመርያ ላይ በቻይና ግዛት በአንድ ተራራማ አካባቢ አቋማቸው የሰውን ልጅ የሚመስል ቁመታቸው ከሰው ቁመት በጣም በብዙ ልዩነት የረዘመ ፍጡራን መገኘታቸውን ሻንጋይ የተባለው ጋዜጣ በአምዱ ይዞ ብቅ ብሎ ነበር:: ጋዜጣው እንዳሰፈረው ከሆነ ፍጡራኑ አቋማቸው የሰውን ቢመስልም አካላቸው በጸጉር የተሸፈነና ጸጉራቸው ከሰውም ሆነ ከእንስሳ እንደማይመሳሰል ያብራራል::

ስለ ፍጡራኑ ጸባይ ሲጠቅስም በጣም ፈጣንና በሰዓት ብዙ ኪሎ ሜትሮችን መሮጥ የሚችሉ የሰው የሚመስል ሳቅ ለረጅም ጊዜ የሚስቁ ናቸው ይላል:: እነዚህ ፍጡራኖች ከሰው ዝርያ የተዳቀሉ ናቸው የሚል መላምት በወቅቱ እንደ ነበር አስታውሳለሁ::"

"እነዚህ ፍጡራኖች በአሁን ወቅት ሊኖሩ ይችላሉ? ከሆነስ በየትኛው ክፍለ ዓለም ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል?"አለ ኢንጂነሩ::

"ስለነዚህ ፍጡራን መኖሪያ በትክክል የተቀመጠ ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ለማግኘት ብዙ የተደከመበት ቢሆንም ከግምት በስተቀር ይህ ነው ተብሎ የተረጋገጠ መረጃ ማግኘት አልተቻለም:: ለምን ቢባል መኖርያቸውን ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን ይዘትና ቅርጽ ጭምር እንደ ፈለጉ መለዋወጥ ስለሚችሉ ፍጡራኑ የእነሱ ዲቃላ ሳይሆኑ አይቀሩም ተብሎ ታምኗል::"

"በተደጋጋሚ ብቅ የሚሉት ፍጡራንን ምንነት ለማወቅ የተደረገው የሳይንስ ሙከራ እስከ አሁንም ድረስ ውጤት ማስገኘት አልቻለም የሚል መላምት አለ:: ከሰው ልጅ ጋርም ስለአላቸው እሉታዊ አለዚያም አወንታዊ ክስተት ለመረዳትም የሰው ልጅ በአገኘው መጠነኛ የእውቀት ብልጭታ የእነሱን ምንነት ለመረዳት የተለያየ ሙከራ ማድረጉ ይታወሳል::

በሳይንስ ያገኛቸውን ዘመናዊ መሣርያ በመጠቀም ስለነሱ ለማወቅ አእምሮን ፈታኝ የሆነ ትንቅንቅ ፈጥሮ እየታገለ ብዙ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ ለሰው ልጅ አእምሮ ፈተና ሆነው የቀሩት ክስተቶች ምንድናቸው ከየትስ ይመጣሉ? ከዚህች መሬት አለዚያም በምድር ላይ ከሚገኘው ሰው የሚፈልጉት ነገርስ ምንድነው? እነዚህ ሁሉ በዘመኑ የቴክኖሎጂ መሣርያ ተለይተው ያልታወቁ የሰው ልጅ ፈታኝ የአእምሮ እና የመንፈስ ፈተናዎች ሆነው በርካታ ዘመናትን በመሻገር ከዛሬ ላይ ደርሰዋል፡፡ በእስከ ዛሬው ጉብኝታቸው በሰውና በመሬት ላይ ያደረሱት ክፋትና ጥፋት ባይኖርም አንድ ቀን ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት አለ፡፡

ራሳቸውን በፈለጉት መንገድ የሚቀያይሩት እነዚህ ፍጡራኖች መነሻቸው ከየት ነው? ምንስ ይመስላሉ? ከግምት በዘለለ እስከ አሁን ምንም ማረጋገጫ የለም፡፡ ወደ ምድር በሚያደርጉት ምልልሳቸው የከፋ ጉዳት ባይደርስም በፍርሃት ማስበርገጋቸው አልቀረም፡፡ ስለ ፍጡራኑ ይዘትና ቅርጽ ብዙ የተጻፉ መረጃዎች የወጡ ቢሆንም በትክክለኛነት ይህ ነው ተብሎ የተረጋገጠ መረጃ ለመስጠት አልተቻለም፡፡ መንግሥታትና የሃይማኖት ሊቃውንትም የሚመሩት ሕዝብ በስጋት ውስጥ እንዳይወድቅ የተለያየ ስያሜ እየሰጡ የማረጋጋት ሙከራ አድርገዋል፡፡ እነዚህ በሥልጣኔአቸው የተራቀቁት ፍጡራን ሱናሚን የመሳሰለውን የባህር መናወጥ በማስነሳት አህጉር አቋርጦ እንደ ነፋስ እንዲጋልብ ለማድረግ የሚሳናቸው አይደሉም፡፡ እንደ ቤት ግድግዳ ቀጥ ብሎ የሚጋልበው የባህሮች ማእበል በነፋስ ግፊት ነው ብሎ ለማመን እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ የመአበሉች እንቅስቃሴን ትእይንት ስንመለከት አንድ ኃይል እንዳለ እንረዳለን፡፡

"ኢየሱስ ክርስቶስ ማእበሉን ገሰጸው" የሚለውን በወንጌሉ ስንመለከት ብዙ ነገሮችን እንድንገምት ያስገድደናል፡፡ ክርስቶስ የሚገስጸው አንድ ረቂቅ የሆነ አካልን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የሰው ልጅ ባልደረሰባቸው ፕላኔቶች የሠለጠኑ ፍጡራን መኖራቸው እርግጥ ስለ መሆኑ ሳይንስ የራሱን ግምት የሰጠ ቢሆንም ይህ ነው ተብሎ በመረጃ የተደገፈ ማረጋገጫ ለመስጠት ገና ብዙ መሥራትን ይጠይቃል፡፡ ሁኔታው ወደ መንፈስነት በመለወጡ ይመስላል ቀስ በቀስ ፍርሃት እየነገሰ ነው፡፡ በሌላ በኩል ቬኑስ በተባለችው ፕላኔት እንደሚኖሩ የሚጠቁም ያልተጣራ የጽሑፍ መረጃ አለ፡፡ እሱም ቢሆን በግምት የተጻፈ እንጂ ታምኖበት የተሰጠ ማረጋገጫ እንዳልሆነ ምሁራኑ መልስ ይሰጣሉ፡፡

ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ መርከቢቱን ማእበል ሲያናውጣት ነፋሱን ገሰጸው ማእበሉም ጸጥ አለ ይላል፡፡ የሚገሰጸው ሕይወት ያለው አካል እንጂ ግኡዝ ነገር አይደለምና ማንን ገሰጸ የሚል ጥርጣሬ አለ፡፡





በሌላ በኩልም ጆን ላንድ ግዶምና ዋትስ የተባሉ ግለሰቦች በፍጡራን ጥሪ እየተደረገላቸውና በእንግድነት ተጋብዘው መኖሪያቸው የሆነችውን ቬኑስን መጐብኘታቸውን ተናግረዋል፡፡ ከአስጐበኙን በኋላ ያለ ምንም ችግር ወደ ምድር ተመልሰናል ማለታቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡"

"ስለነዚህ ፍጡራን ሳይንስ ያቀረበው ዘገባ እውነትነት አልነበረውም እያልከኝ መሰለኝ፡፡ የፍጡራኑ መኖሪያ ማርስ ልትሆን እንደምትችል ያረጋገጠ መረጃ በየጊዜው ወጥቷል፡፡ አይደለም እንዴ?" አለው ዶክተሩን፡፡

"እንዳልከው በማርስና በቬኑስ ላይ ይኖራሉ የሚል የተረጋገጠ ሳይሆን በግምት የተሰጠ የባለ ሙያዎች መረጃ በየዘመናት ወጥተው እንደ ነበር ከላይ ጠቅሼልሃለሁ፡፡ ያም ሆኖ በነዚህ ፕላኔቶች ላይ ያለው ሙቀት እንደ ሥጋ መጥበስ ስለሚችል ፍጡራንን አያኖርም፡፡ ስለዚህ ዋትስ በቬኑስ ላይ ዩፎዎች ይኖራሉ ብሎ በግምት የሚሰጠው መረጃ ትክክል አይደለም የሚሉ ብዙ ማስተባበያዎች በወቅቱ ወጥተው የነበረው ለዚህ ነው፡፡ በርግጥም እነዚህ ፍጡራን ሕይወት ያላቸው በመሆናቸው ምንም አየር በሌለበት ቦታ ለመኖር ሊቸገሩ ይችላሉ የሚለው መልስ መሆን ይችላል፡፡

የት እንዳሉና ምን እንደሚመስሉ ለማጥናት ሙከራ ያደረጉት የሶቬትና የአሜሪካን የመንኮራኩር ባለ ሙያዎች ቫይኪንግ አንድና ቫይኪንግ ሁለት የተባሉ መንኮራኩሮችን በ1976 ዓ.ም ወደ ህዋ ልከው መንኩራኩሮቹ በተሳካ ሁኔታ ማርስ ላይ ለማረፍ ቢችሉም ፍጡራኑ ስለ መኖራቸው የሚጠቁም አንድም ፍንጭ ሰጭ መልእክት ወደ ምድር ለማስተላለፍ አልቻሉም፡፡ ከፀሐይ በአራተኛ ደረጃ በቬኑስ እንደሚገኙ በሳይንሳዊ ልብ ወለድ መጽሐፍ የተፃፈው ታሪክ ለአሜሪካን ሕዝብ በሬዲዮ በትረካ መልክ እንዲተላለፍ ተደርጎ ነበር፡፡ ሕዝቡ በከፍተኛ ሽብር ውስጥ በመውደቁ ወድያውኑ እንዳይተላለፍ ተደርጓል፡፡

የሰውን ልጅ በጠላትነት የሚመለከቱ ርኩስ መናፍስት ሊሆኑ ይችላሉ የሚለው ፕሮፖጋንዳ በእምነት ሰዎችና በመሪዎች በመስተጋባቱ የቀረበው ትረካ እንዲቋረጥ አድርጓል፡፡

ከኔዝ አርኖልድ የተባለ ግለሰብ ዋሽንግተን ባይነር በተባለው ተራራ ላይ አንድ በራሪ ዲስክ በአየር ላይ ሲንሳፈፍ አየሁ ብሎም ነበር፡፡ ዩፎዎች በማርስ መኖራቸውን እንደ ማረጋገጫ የሰጠውም ማርስ ከመሬት ጋር ትይዩ በመሆኗ የዩፎዎች በረራ በብዛት ሊታይ ችሏል የሚል ነው፡፡ የዚህ ተመራማሪ ገለጻ እየተዘነጋ የዩፎችም ወደ ምድር መምጣት መቀነስ ተደማምሮ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ዓመታት በመዘግየት የተረሳ ቢመስልም ኖርማንና ሌሎችም ሰዎች በዩፎች ተጠልፈው ስለ ተወሰዱ የመላምት ምርምሩን ከምን ጊዜውም በላይ የተወሳሰበ አድርጎት የዩፎዎች የመኖሪያ አድራሻ በማርስ ላይ ብቻ ሳይሆን ከምድር ውስጥ ወይም ደግሞ ከየብስ በታች በጥልቅ ውቅያኖስ ውስጥ ነው የሚል የመላ ምት አስተያየት

መስጠት ተጀመረ። ተጠሳፊዎቹ እንደ መነሻ የወሰዱት ነጥብም ቤርሙዳ የተባለውን የባህር ክልል መሆኑን ዘገባው ይጠቁማል።

ቤርሙዳ እስከ ዛሬም ድረስ መልስ ያልተገኘለትና አያሌ ተመራማሪዎችን ከፈተና ውስጥ የከተተ የባህር ሰርጥ ሲሆን በዚህ አካባቢ የቀዘፉ መርከቦችም ሆኑ በዚያ አቅጣጫ የበረሩ አውሮፕላኖች ካሰቡት ሳይደርሱ የውኃ ሽታ ሆነው በወጡበት ቀርተዋል። በዚያ ክልል ሲደርሱ ኮምፓሱ ይጠፋባቸዋል የሚል ያልተብራራ መረጃ የወጣ ሲሆን ኮምፓሱ እንደጠፋም ክልሉ በጉም መሰል ብርሃን ይሸፈናል ነው የሚሉት። የመርከብ ሠራተኞቹም ሆኑ የአውሮፕላን አብራሪዎቹ የአደጋ ጥሪ መሣሪያዎቻቸውን ጭመር ብልሽት ስለሚገጥመው የአደጋ ጥሪም ሳያደርጉ ነው የተሰወሩት ባይ ናቸው። እንደሚሉት ከተሰወሩት አውሮፕላኖችም ሆነ መርከቦች በወቅቱ የተደረገ የአደጋ ጊዜ ጥሪ ተመዝግቦ አልተገኘም።

"መርከብና አውሮፕላንን ያህል ነገር በሚወስዱበት ወቅት እንዴት እና በምን መንገድ እንደ ሆነ መረጃ ማግኘት ያልተቻለው ቀድመው መስመሩን ስለሚያቋርጡት ነው የሚለው ግምት ያስኬዳል። ስለ ተጠለፉት መርከቦችም ሆነ አውሮፕላኖች የሳይንስ ውጤት የሆነው መሣሪያ አልደረሰበትም። የቤርሙዳን ምሥጢር ለማጥናት የተሰለፉት የምርምር ባለ ሙያዎችም ቢሆኑ የሰጡት አስተያየት እየደረሰ ያለው የጠለፋ ተግባር የዩፎዎች ውንብድና ነው ከማለት በዘለለ ትክክለኛ ፍንጭ መስጠት አልቻሉም።"

ዩፎሎጂስቶች እንደሚገምቱት ከሆነ ለበርካታ ዓመታት አድራሻቸው ጠፍቶ የተሰወሩት መርከቦችም ሆኑ አውሮፕላኖች በቤርሙዳ ውስጥ ባሉት የሠለጠኑ ፍጡራን እየተጠለፉ ነው ባይ ናቸው። ይህ ስፍራ የሚገኘውም ከአሜሪካን በስተሰሜን አቅጣጫ በአትላንቲክ ውቂያኖስ የባህር ክልል ውስጥ ነው። በሺህ የሚቆጠሩ መርከቦችንና በብዙ አሥርታት የሚገመቱ አውሮፕላኖችን የውኃ ሽታ አድርጎ በወጡበት በማስቀረቱም "የአትላንቲክ መካነ መቃብርና የዲያብሎስ ትሪአንግል እንዲሁም የሁዱ ባህር የሞት ቀጠና ተብሎ የአስፈሪዎች አስፈሪ ስም የተሰጠው ይህ የባህር ክልል የጃፓንን የባህር ክልልም የሚያዋስን ነው። ቀደም ሲል የነበረው አትላንት የተባለው የሥልጣኔ ስፍራ ወይም አህጉር በአትላንቲክ ውቅያኖስ ሊሰምጥ የቻለው በነዚሁ የሠለጠኑ ፍጡራን በተወሰደ የኒውክለር ፍንዳታ ነው ባይ ናቸው ተመራማሪዎቹ። እነሱ እንደሚሉት ከሆነም አትላንቲስ የተባለው አህጉር ከአትላንቲክስ ውቅያኖስ በታች የሚገኝ ሲሆን ፍንዳታው ደርሶበት በአትላንቲክ ውቅያኖስ ከመዋጡ በፊት የሠለጠነ አህጉር ነበር የሚል ነው።

"ኤድጋር ካይስ የተባለው አሜሪካዊው ትንቢተኛ አትላንቲስ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ በላይ ተንሳፍፎ ይታያል በማለት በ1940ዓ.ም ተንብዮ እንደ ነበር መረጃ አለ። ከሀያ ስምንት ዓመታት በኋላ ትንቢቱ ተፈጽሞ በጣም ግዙፍ የሆኑ ቋጥኞች ጭምር ከውቅያኖሱ በላይ





እስከ አራት ጫማ ድረስ ከፍ ብለው አግጥጠው መውጣታቸውን በርካታ ጸሐፊዎች ለሕዝብ አስነብበው ነበር። ከውቅያኖስ በታች በተደረገም ምርምር በርካታ መንገዶችና የከተማ ወይም የሕንፃ ፍርስራሾች ማግኘታቸውን ተመራማሪዎች ይገልጻሉ። በነገራችን ላይ ከብዙ ዘመናት በፊት በሰሜን ሸዋ ደብረ ብርሃን ላይ ከሰማይ ወርዶ የነበረ የብርሃን ወይም የእሳት ኳስ በመጨረሻው ዘመን ጅራታም ኮከብ ይታያል የሚለውን የትንቢት ቃል አጠናክሯል የሚሉ ብዙ መጽሐፍትም ተጽፈዋል። ደብረ ብርሃን የስም ስያሜዋን ያገኘችው ከዚህ ብርሃን መሆኑን የታሪክ ድርሳኗ ያስረዳል። በኢትዮጵያ በደቡብ ክልል አንድ የመሬት አካል በኦሞ ባህር ላይ እየተንሳፈፈ ሲመጣ መታየቱን በመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ ተደርጎ ነበር። የመሬቱ አካል ከየት እንደ መጣ ከዘርፉ ባለ ሙያዎች የተሰጠ ማረጋገጫ የለም። ከአሥራ አምስት ዓመት በፊትም በዚሁ በደቡብ የኢትዮጵያ ክልል በአዋሳ አካባቢ በሚገኙት ሦስት ወረዳዎች በርካታ የእሳ መንጋ መዝነቡ ይታወቃል። በዚህ ዙሪያ የባለ ሙያ ጥናት ስለ መደረጉ የማውቀውና የሰማሁት ባይኖርም በአሳዎቹ ሬሳ የመኪና መንገዱ እስከ መዘጋት ደርሶ እንደ ነበር በወቅቱ በጀርመንና በአሜሪካን ሬድዮ ጣቢያ በስፋት ተዘግቧል።

"በአንድ ዘመን የሠለጠነችው አትላንቲስ በአትላንቲክ ውቅያኖስ ከመዋጧ በፊት የመሬት አካል እንደ ነበረች አያጠራጥርም። የሰው ልጅ አሁን ከሚኖርባቸው ሰባት አህጉራት መካከልም ስምንተኛው ነበረች የሚል ግምት አለ። የግሪኩ ፕላቶ ቲማኡስና ክሪሽያስ በተባሉት መጽሐፎቹ ስለዚህ ስፍራ ብዙ ነገሮችን አስፍሯል። ግብጽን ሊጎበኝ በሄደበት ወቅት በአንድ መንፈሳዊ መነኩሴ ስለ አትላንቲስ በዝርዝር እንደ ተገለጠለት ነው የሚያብራራው። የሄርኩለስ ምሰሶ የጂብራልታል የባህር ወሽመጥ ተብሎ ይጠራ በነበረው በአፍሪካ በሰሜን ምዕራብ ይገኝ የነበረ መሬት ሲሆን የኢስያን አህጉር ያህል ስፋት እንደ ነበረውም ይታመናል። በዚህ ስፋራ ከብዙ ዘመናት በፊት ባለ ቀይ ቆዳ ሕዝቦች ይኖሩበት ነበር የሚል ግምት አለ። "ፓሲይዶኒስ ተብሎ ይጠራ የነበረ ከተማ ስለ መኖሩም የተገኘው መረጃ ይጠቁማል ባይ ናቸው ተመራማሪዎቹ። ምድርን በተደጋጋሚ መጎብኘታቸውና አንዳንድ ጊዜም ጸብ የመተንኮሳቸው ሁኔታ የዓለምን ሕዝብ እያስበረገገው በመምጣቱ ስለነሱ የሚደረገው ምርመር በተናጠል አንዳንድ ጊዜም በህብረት በመቀጠሉ የነሱ ጉዳይ አጓጊ እየሆነ እስከ መምጣት እንደ ደረሰ ይታወቃል።

ከእይታ ውጭ ቢሆኑም የመኪና ሞተር በድንገት ሲጠፋና የሬድዮ መስመር ሲቋረጥ፣ የቴሌቪዥን ምስል ተርገብግቦ ሲጠፋ፣ የእጅና የግድግዳ ሰዓቶች ሥራቸውን ሲያቆሙ፣ እንደዚሁም የስልክ መስመር በተለየ ድምጽ ሲሞላ አለዚያም እንግዳ በሆነ ድምጽ ሲቆራረጥ ፍጡራን ወደ

ምድር እየቀረቡ መሆኑን የዩፎ ጥናት ባለ ሙያዎች ያምናሉ፡፡

ስፍራውን ለቅቀው መሄዳቸውን የሚያረጋግጡትም የተቋረጡ የኤሌክትሮኒክስ መሣርያዎች ሥራቸውን እንደ ገና በሚጀምሩበት ወቅት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በ1965ዓ.ም የአሜሪካን ስምንት ከተማዎችና ካናዳም ጭምር መብራቶች ተቋርጠው ሕዝብ በጨለማ መዋጡን በወቅቱ ለሕዝብ ይፋ የወጡ መረጃዎች ተናግረዋል፡፡ በኒዮርክ የምድር ውስጥ ባቡሮች የሚንቀሳቀሱበት ኤሌክትሪክ ተቋርጦ ሞተራቸው ስለ ጠፋ በሺህ የሚቆጠሩ መንገደኞች በጨለማ ውስጥ እንዲቆዩ ተገድደዋል፡፡ የረጃጅም ሕንፃ አሳንሰሮችም ሥራቸው ስለ ተቋረጠ በአሳንሰሩ ውስጥ የነበሩ ሰዎች በዚያው ተንጠልጥለው በርካታ ሰዓታትን አሳልፈዋል፡፡ ድመቶች እርስ በራሳቸው ከፍተኛ ጠብ ሲፈጥሩ የጋማ ከብቶች ሲደነብሩና ዶሮዎች ክንፋቸውን እያማቱ በአጥር ሲዘሉ እነዚህ ሁሉ ለነሱ መምጣት ምልክት ናቸው፡፡

"በነገራችን ላይ ሱናሜ በተነሳበት ወቅትም እኮ የእንስሳት መደንበር ተከስቶ ስለ ነበር በተለይ ዝሆኖች ከአካባቢው ለቅቀው መሸሻቸውን ያዩ ሰዎች ከስፍራው ለቅቀው ስለ ነበር ከውኃ መጥለቅለቅ ሲድኑ ችለዋል፡፡ የሚል ዜና በወቅቱ ሰምቼ ነበር" አለ ኢንጂነሩ፡፡

"በዚህ ዙሪያ የተነሳ ነገር ባለ መኖሩ የምትለውን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡ በሌላ በኩል ደራሲው "ከበራሪ አካሎች በስተጀርባ" በተባለው መጽሐፉ ብዙ ነገሮችን የዘረዘረ ሲሆን ሶስት ዩፎዎች በአሜሪካን አየር ኃይል ተይዘዋል የሚል መረጃ አስቀምጦ ነበር፡፡ በራሪው አካል በአየር ኃይሉ በተጠለፈበት ወቅትም በውስጡ አርባ ስምንት ፍጡራን እንደ ነበሩ ነው መጽሐፉ የሚያትተው፡፡

በሲሲሊ ማፍያዎች የተሠራ እንደ ሆነ የሚጠረጠረው ዩፎ ወይም በራሪ አካል በአየር ላይ ሲንሳፈፍ ታይቶ በወቅቱ የኃያላኑን ጦር ሰፈር ለመሰለል ሂትለር አሰሯቸው በማለት የሐሰት መረጃዎች ተላልፈውም ነበር፡፡

በ1959 ዓ.ም እርስ በርሳቸው ተጋጭተው አንደኛው በራሪ ወደ መሬት በመውደቁ በመንኮራኩሩ ውስጥ ሰው የሚመስል ፍጡር የተገኘ ሲሆን ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ሲወሰድ ሕይወቱ ማለፏን በወቅቱ ምርመራውን ያደረጉት ዶክተሮች ይናገራሉ፡፡ ዶክተሮቹ እንደ ተናገሩት ፍጡሩ የለበሰው የብረት ጥሩር አለዚያም የሰውነት መከላከያ ብረት ነበር የሚል ነው፡፡ በአንደኛው የሰውነት ክፍሉ በኩል ሰውን ሲመስል የእጅና የእግሩ ጣቶች ከሰው በተለየ መልኩ በርካታ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ የውስጥ አካሉን በተመለከተም ከሰው የተለየ ነው ባይ ናቸው፡፡ የአሜሪካን የጠፈር ምርምር ናሳ ብዙ ነገርን የተመለከተ መሆኑ ቢታመንም ለሕዝብ ይፋ ሳያደርግ የራሱ ምሥጢር አድርጎት ቆይቷል የሚል ግምት አለ፡፡ ናሳ ለምን በምሥጢር ለመያዝ እንደ ፈለገ በውል የተጠቀሰ ምክንያት የለም፡፡





የመንኮራኩሮቹ አብራሪዎችም መግለጫ እንዲሰጡ ተጠይቀው ፍቃደኛ ባለ መሆናቸው የአሜሪካን የስለላ ድርጅቶች ሲ አይ ኤ ምሥጢሩ ይፋ እንዳይወጣ ከልክሏል የሚል አስተያየት አለ፡፡ በ1950ዓ.ም ሜክሲኮ ወድቆ በነበረው የበራሪ አካል ውስጥ የተገኘው ፍጡር ሀያ ስምንት ኢንች ያህል ቁመት ያለውና በጣም ስስ ልብስ የለበሰ የላስቲክ ቡትስ የተጫማ የደረቱ አጥንት እንደ ማገር የገጠጠና ምታሪ የሥጋ ዘር የሌለው የጎድን አጥንቶች አንድ ሁለት ተብለው መቆጠር የሚችሉ ናቸው የሚል ነው፡፡"

በ1897ዓ.ም በቴክሳስ አካበቢ ወደቀ የተባለውም በ1908ዓ.ም በሶቭየት ወደቀ ከተባለው ዩፎ መዛመድ ያለ መቻሉ የዩፎችን የተለያየ ባህርይም ይጠቁማል፡፡ በሳይቬርያ አካባቢ የወደቀው ዩፎ በመጀመሪያ እንደ ተሰማ የኑክልየር ፍንዳታ ተብሎ ስያሜ ተሰጥቶት እንደ ነበር ይታወሳል፡፡ በ1957 በብራዚልና በ1947 ዓ.ም በሲውዲን የባህር ክልል ውስጥ በርከት ያሉ ዩፎዎች መውደቃቸው የተዘገበ ሲሆን በተደረጉት ጥናቶች ከህዋው ጋር የሚያመሳስላቸው ከለራቸው ጭምር ከቴክኖሎጂ መሣርያው የሚሰውራቸው የሚል ግምትም አለ፡፡ በዚህ ባህሪያቸውም እነሱ ለመታየት ካልፈቀዱ በቀር ለማየት የማይሞከርና የሚረጩት የብርሃን ጨረርም ይህችን ዓለም ያነዳታል ተብሎ ይታመናል፡፡ የሰው ልጅ ያደረጋቸው ሙከራዎቹ ውጤት ባለማስገኘታቸውም የምርምር ዘርፉን በመቀየር የሰውን ዘር በተለየ ቅርጽና ይዘት በጄኔቲክ ለመፍጠርና እነዚህን ፍጡራን ለማወቅ መንቀሳቀስ የግድ መሆኑ እየታመነበት መጣ፡፡ በዚህ መልኩ ጉዳዩ ትኩረት አግኝቶም በአሜሪካን አስተዳደር በጄኔቲክ የሰውን ልጅ አፈጣጠር ተቋምን ለማቋቋም ለወቅቱ አስተዳደር ከሳይንቲስቶች ጥያቄ የቀረበውም በዚህ ወቅት ላይ ነበር፡፡ የአሜሪካን አስተዳደር በበኩሉ እነዚህን ፍጡራን ማንነታቸውን ለመረዳት የሚችል የሰው ዝርያ ለማግኘት ከተቻለ ተቋሙን በማንኛውም መንገድ ለመርዳት ፍቃደኛ በመሆኑ የቡሽ አስተዳደር እስከተተካበት ጊዜ ድረስ የምርምር ተቋሙ በመንግሥት እየተደገፈ ሲሠራ ቆይቶ ከቡሽ በኋላ በተደረገ ተቃውሞ ምርምሩ እንዲዘጋ ተደርጓል፡፡ ከተዘጋ በኋላም ሳይንቲስቶቹ የት እንደደረሱ ሳይታወቅ ለበርካታ ዓመታት ተሰውረው ለመኖር ግድ ሆኖባቸዋል፡፡"

"ተቋሙ የተዘጋው በቡሽ አስተዳደር ጊዜ ነው እያልከኝ ነው" አለ ኢንጂነሩ፡፡

"እንደዚያ ነው፡፡ የታላቁ የቡብ አስተዳዳር ተቋሙን እንዲዘጋ ከአደረገ በኋላም ሳይንቲስቶቹ አገር ጥለው እንዲሰደዱ ልዩ ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል፡፡"

"ተቋሙ እንዲዘጋ የተደረገበት ምክንያቱ ምን ነበር?" አለው፡፡

"ከተለያዩ የእምነት ተቋማት በደረሰው ተቃውሞ ነው፡፡ የሰውን ዘር

በጄኔቲክ ማራባት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቃውሞን አስከትሎ እንደ ነበር ይታወሳል።"

"ፈርቶ ነው የአሜሪካን መንግሥት ተቋሙን የዘጋው እያልከኝ መሰለኝ" አለ ኢንጂነሩ።

"እንዱ እሱ ቢሆንም የቡሽ አስተዳደር በራሱ የሰውን ዘር በተለየ ዘዴ ማራባት የሚለውን የሳይንስ ቀመር አልተቀበለውም ነበር።"

"ምርምሩ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ እስከ አሁን ድረስ የተፈለገው ዓይነት የሰው ፍጥረት ይገኛል የሚል እምነት ነበረህ?" አለ ኢንጂነሩ።

"እርግጠኛ አይደለሁም" አለ ዶክተሩ።

"ከአሁኑስ የምርምር ሂደት ውጤቱ ምን ይሆናል ብለህ ትጠብቃለህ።?"

"ለሱም ቢሆን በቂ መልስ የለኝም" አለ ተመራማሪው።

"አንዳንድ ጊዜ ምን እንደሚሰማኝ ታውቃለህ?" አለው።

"የሰው ልጅ ራሱ በፈጠረው ፍጡር ተበልቶ እንዳያልቅ እሰጋለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን ብናነብ ዓለም ብዙ ክስተቶችን እንዳስተናገደች እንረዳለን። ከነዚህም በመጽሐፈ ሄኖክ የሰፈረውን መመልከት ይቻላል። ያዘመን የሰው ልጅ የሠለጠነበት ዘመን ነበር ለማለት ይቻላል። የጦርና የተለያዩ መሣሪያዎችን ከመፈልሰፍ አልፈው ሰውን በቅሎ በቅሎውን ሰው እስከማድረግ ደረጃ እውቀታቸው መጥቆ እንደ ነበር ይህ የመጽሐፍ ክፍል በሰፊው ያብራራል። በወቅቱ ቁመታቸው ሦስት ሦስት ሺህ ክንድ የሚደርሱ ሰዎች ተፈጥረው ሕዝቡን በልተው መጨረሻቸውንም በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቤ ነበር።"

"በርግጥ የምትለውን እኔም እጋራለሁ።

"መንግሥታት ፍለጋቸውን ያጠናከሩት ይህ ሁኔታ ስጋት አሳድሮባቸው ይሆን?"

ዶክተሩ ትክሻውን አነጠረ "አይታወቅም።"





# ምእራፍ ሀያ ስድስት

የመረጃ መኮንኑ ከአንድ የተዘጋ ክፍል አጠገብ እንደ ደረሰ ወደ ኂላው ዞረና ከአጠገቡ የነበሩትን ሁለት የጸጥታ ፖሊሶች ገልመጥ አደረጋቸው። በጥንቃቄ እንደ ቆሙ ናቸው። በኩራት ትክሻውን ከፍ አድርጎ የተዘጋውን በር በአገጩ አመለከታቸው። የጸጥታ ፖሊሱ መዝጊያውን ገፋ ሲያደርገው ተከፈተ። የጸጥታ ፖሊሶቹ በጥርጣሬ ተያዩ።

የክፍሉን ግማሽ በያዘው አልጋ ላይ የተያዘው ትወና ያልተለመደና ያለ ሰዓቱና ያለ ስፍራው እየተሠራ ያለ ቲያትር ነው። ምን እየተደረገና እየተፈጠረ ነው በየራሳቸው ራሳቸውን ጠየቁ። በጀርባው እንደ ተንጋለለ ወፍራም እግሮቹን ግራ ቀኝ በርግዶ የተኛውን ሰው መሰል ፍጡር ደጋግመው ተመለከቱት። በተደረገበት ወረራ ደንታ ሳይኖረው ጭዋታውን እንደ ቀጠለ ነበር። በአየር የተሞላ ፊኛ የሚመስሉት እጆቹ ግራቀኝ ተመንቅረው የትክሻውን ውኃ ልክ እንደ ጠበቁ ተዘርግተዋል። እግሮቹም በተመሳሳይ አኳኋን ተከፍተዋል። ግዙፍ ሰውነቱ ላይ ስትታይ ከቢራቢሮ የማትበልጥ ልጅ ተሳፍራዋለች። ከጭንቅላቷ ላይ የወረደው ጸጉር ጡትና ፊቷን ከመሸፈኑ በቀር የጡት ማስያዣ እንኳን የላትም።

መሣሪያ የደገኑባቸውን ወታደሮች ቀና ብላ አይታቸው ሥራዋን ቀጥላለች። ልዩ የሆነ ድምጽ ከጉሮሮዋ እያስወጣች ነው የምትንቀሳቀሰው። ስልቷን እየጠበቀች በጥንቃቄ ስትሽከረከር በጸጥታ ተጋድሞ ከሷ ወደሱ እየመጣ ያለውን የሰውነት ሙቀቷን የሚያደምጠው ግዙፍ ሰው ዓይኖቹ እንደ ተጨፈኑ ናቸው። በእሷ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሁለት ልጆች ከፊት ለፊት ከአልጋው በግራና በቀኝ እርቃነ ሥጋቸውን ቆመው ሰውነታቸውን እያሻሹ ዓይናቸውን በስሜት ጨፍነዋል። እንቅስቃሴያቸው ምትሃታዊ ነው። ከጸጉራቸው ይነሱና አንገታቸውን፣ ጡታቸውን፣ ደረታቸውን፣ ሆድና እንብርታቸውን እየዳሰሱ ተንሸራተው ጭልጥ ብለው ወደ ጥልቁ ሲወርዱ አንዳች ጩኸት ያሰማሉ። በጥርሳቸው መካከል የሚያስወጡት ድምጽ እጅግ የተለየ ነው። በራሳቸው ንክኪ የራሳቸውን ስሜት ቀስቅሰው ራሳቸውን ወደ ከፍተኛ እብድነት የተለወጡ ንኮች ነው የሚመስሉት።

ከአልጋው ላይ የተዘረረው ግዙፍ ሰው የሁለቱን ልጆች የተለየ እንቅስቃሴ አሻግሮ ለመመልከት አልፎ አልፎ ትላልቅ ዓይኖቹን በኃይል ይከፍታቸዋል፡ የመስኮት ያህል ስፋት ያላቸው የመልክ ማያ መስታወቶች በአልጋው ትይዩ ተሰቅለዋል። ወፍራሙ ሰው እነሱን እየተመለከተ አልፎ አልፎ የሚያወጣው ድምጽ ለጆሮ ደስ የሚል አይደለም። በአስፈሪ ሁኔታ ያንቋርራል። የጸጥታ ሠራተኞቹ "በሚያዩት ተደናግጠው በዓይናቸው

ተነጋግረው ተግባቡ። ይህንን ትእይንት ማየት ያለበት ከውጭ እየጠበቃቸው ያለው አለቃቸው ነው። መግባትና ድራማውን ማየት አለበት። ያዩትን ቢነግሩት በቂ አይሆንም። በዓይኑ አይቶ መፍረድ ይኖርበታል። ከበሩ አጠገብ የነበረው ፖሊስ ወጣና የመረጃ መኮንኑን ሲጠራው ተከትሎት እየተቻኮለ ወደ ክፍሉ ገባ። የተመለከተው የጠበቀውን አልነበረም። በድንጋጤ ዓይነት ስሜት ተውጦ እንደ ቆመ በክፍሉ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ተመለከተ። በሕልሙ ቢሆን በተደሰተ ነበር። ጨረባ መስላ ከሰውየው ላይ ወደ ተፈናጠጠችው ፍጥረት አፈጠጠ። ትዕግሥት አልነበረውም። እንደ ዶሮ ማንቁርቷን አንቆ ከወለሉ ላይ ወረወራት።

አምላኬ ምንድነው የማየው ነገር? አፉን በመዳፉ ይዞ አጉተመተመ ዘሩባቤል።

"ልብሳቸውን እንዲለብሱ አድርጉ" አላቸው ፊቱን ወደ በሩ መልሶ።

በዚች አገር ምን እየተፈጠረ ነው ያለው? በጋጠወጦቹ የፊልም እስክሪን አይቶት የነበረው በራሱ በወገኖቹ እየተፈጸመ ነው። ከዚህ ትውልድ ምን ይጠበቃል። እንስሳ ምን ጊዜም ያው እንስሳ ነው። ሥነ ምግባር የጎደላቸው ድርጊቶች በብዙ ዓለማት በየሰዓቱ ሊከናወኑ ይችላሉ። ከኢትዮጵያ እምነትና የባህል አስተሳሰብ አንጻር ግን ከወሬ በዘለለ በድርጊት ሲከናወኑ መመልከት ትልቅ የሞራል ውድቀት ነው። አስነዋሪ ድርጊት መመልከት ስሜትን ይነካል። እምነትና ባህል ለሌላቸው ሕዝቦች እንደ መዝናኛ ሊወሰድ ይችል ይሆናል።

የእምነትና የባህል ድንኳን የሆነችው ሀገር በዚህ መልኩ መጥፋት የለባትም። እየተደረገ ያለው ጥፋት ነው።

የሴትነት ኩራትና ክብራቸውን አዋርደው እንደ ሸቀጥ ለገበያ ማቅረብ ሁለትና ሦስት እየሆኑ ከአንድ ወንድ በጋራ መሰሰን በፍፁም ከጤነኛ አእምሮ የሚመጣ አይደለም። ማበድ ጀምረዋል። ማንኛውም ነገር የሚለመደው እንደዚሁ ትንሽ በትንሽ ነው። ዛሬ አንድን ወንድ በጋራ ነገ ደግሞ እንደዚሁ በተመሳሳይ… ከዚያ በኋላ አድማሱን እያሰፋ ይቀጥላል። በአንድ ቤት ውስጥ ከገዛ ሰውነታቸው ጋር እየተዳሩ አንድን ወንድ የሚጋሩ ከሆነ እርስ በርሳቸው የሰውነት ንክኪ ስለአለማድረጋቸው ምን ማረጋገጫ ይኖራል። ይህ ብስብስ በመጨረሻ የሚረካበት እነሱን ግብረ ሰዶም በማሠራት ሊሆን ይችላል። የውሻ ልጅ። እንደ ዱባ እየሰነጠቅሁ እሚወትብኃለሁ። እንደ እርጥብ ስልቻ ረግጥሃለሁ። የለም የለም ብረት አግዬ… መጥበስ ነው ያለብኝ። እነዚህ ማፈሪያዎችስ ምን መደረግ አለባቸው? አሰቃቂ ያላቸውን የቅጣት ዓይነቶች ሲያወርድበት በውስጡ እየዛተ ፊቱን ሲመልስ

"ልብሳቸውን እንዲለብሱ አድርገናል" አለው የጸጥታ ፖሊሱ።

"ምን አልከኝ?" አለ ዘሩባቤል።





"ልብስ ለብሰዋል" አለው ደገመና። አይኑ ልቡናውን ከፍቶ ሲመለከት ሦስቱም ሴቶች አንገት ለአንገት ተጠጋግተው ከወለሉ ላይ ተቀምጠዋል። የለበሱት ታይት ሱሪ ከራቁት የተለየ ባለመሆኑ የውስጥ አካላቸውን ልቅም አድርጎ ያሳያል።

"ምኑን ለበሱት ራቁት ናቸው እንጂ" አለ መኮንኑ። የሥልጣኔያቸው መግለጫ የሆነችው ብርድና ጸሐይ የማትከለክል ቲሸርት እንደዚሁ ስስ የጡት ማስያዣ ከደረታቸው አስረዋል። ተለብሶ ተሙቷል አለ ደግሞ ለራሱ። አንድ ነገር ታወሰውና በምፀት ፈገግ አለ። አራት ኪሎ አካባቢ በእግሩ እየሄደ ነው። አራት ያህል ወጣቶች ናቸው ከፊቱ ያሉት። በማሃል በእጁ ይዞት የነበረው ቁልፍ ይወድቅበትና ጐንበስ ይላል። መቀመጫው ባዶ ነው። ባላውን ሲመለከት ዘገነነው። ዘመነኛው ወጣት ሱሪውን የታጠቀደው ከታፋው ላይ ነበር። ራሱን መቆጣጠር አልቻለም። በጫማ ካልቾ ሲያቀምሰው ሱሪው ጠልፎ ጣለው ሌሎቹ ሽሽት ጀመሩ ሱሪያቸው ተንሸራተተ ሰብስበው ይዘው ፈረጠጡ ራሱን ነጻ ያላደረገ ትውልድ ሀገሩን ይጠብቃል ብሎ ማሰብ የዋህነት መሆኑን ተገነዘበ።

"እከክ ያልብሳችሁ አ አምላኬ። የተረገማችሁ ከንቱ ፍጥረቶች" ሰረቅ እያደረጉ እያዩት ይንሾካሾኩበት ስለነበር እየሰደቡት እንደ ሆነ ገባው። ውሻዎች አለ። በለሆሳስ። ወንዱም ሴቱም ሞራሉን የጣለ ለዋስ ትውልድ።

ትኩር ብሎ ሲመለከታቸው "ወልደው ሳይጨርሱ" የሚለው አባባል ታወሰው በክፍሉ ውስጥ ትንሽ ከተንጎራደደ በኋላ ከአልጋው ላይ የተቀመጠውን ሰው መሳይ ፍጡር አዘቅዝቆ ተመለከተው። ስስ ሸርጥ ጭኑ ላይ ጣል ባያደርግበት ኖሮ ራቁት ገላውን ለማየት ባልደፈረም ነበር። ምንም የሚታይ መልክና ቅርጽ  የለውም። ወፍራም እጆቹን በሰንሰለት ተጠፍሮ ሲመለከት ውስጡ ተደሰተ። እንደ ጉማሬ የወፈረው ቦርጩ ተጣጥፎ እጭኖቹ ላይ በማረፉ አፍረቱን ጋርዶለታል። ወፍራምና ቀይ ከንፈሩ ቁልቁል ተንጠልጥሎ ወርዶ የኮርማ በሬ ዳልጋ መስሏል። ልቅም አድርጎ ሊመለከተው ሞከረ። እንደጣውላ የረዘመ ፊትና ተመሳሳይ አፍንጫ አለው። አስገራሚ ተፈጥሮውን ሲመለከተው ቆየ ልጆቹ አንገታቸውን እንዳቀረቀሩ እንዷ የሌላዋን ጀርባ ይጠብቃሉ። ጥላቻ ይሁን ኃዘኔታ በውል ያልገባው ስሜት ውስጡን ሲበጠብጠው "መልክ ብላሽ…" አለ በድጋሚ። መታጠቢያ ቤት አግብተው እንዲዘጉባቸው ረዳቶቹን አዘዛቸው።

ብርድና ድንጋጤ እየተፈራረቀ ኩርማን ያሳከላቸው ምስኪኖች እጃቸው ላይ በተንጠለጠለ ካቴና እንደተጠላለፉ ወደ ሻወር ቤቱ ሲገቡ በጨረፍታ ሲመለከቱት ውስጡ ተበጠበጠበት። ያልታደሉት እነሱ ወይስ አገሪቱ እራሱን ጠየቀ ዘሩባቤል።

"ከዚህ ደደብ ጋር ትንሽ ማውራት እፈልጋለሁ" ሲላቸው ክፍሉን ለቅቀውለት ወጡና ከበረንዳው ላይ ቆሙ ረዳቶቹ።

"ቁልቁል ተመለከተው። "ምን እየሠራህ ነበር ያለኸው? ከሦስት ሴቶች ጋር ያውም የልጅ ልጆችህ ከሚሆኑ ሕፃናት በአንድ ላይ ወሲብ ስትፈጽም ምን ይሰማሃል? ምን ዓይነት እርካታ ነው የሚሰጥህ? ምን ዓይነት ባህልና እምነት ነው ያለህ? በሰው ልጅ ስብእና ላይ የምትቀልድ ቆሻሻ"

ሰውየው ለሚወርድበት ስድብ ግድ የሰጠው አይመስልም በግዴለሽነት ቀና ብሎ ተመለከተው።

"ለአደረግሁትና ለማደርገው ገንዘብ ከፍዬ እንጂ ያለ ፍላጎታቸው አስገድጀ አይደለም። እውቀውና ተስማምተው ለሚፈጽሙት ዋጋ ተከፍሏቸውና ተደስተው ነው ከኔ ጋር ይህንን ተግባር የፈጸሙት። አስገድጀ የሠራሁት ጥፋት የለም። ባህልና እምነት ለምትለው ያ እኔን እንጂ ማንንም የሚመለከትና የሚያሳስብ ጉዳይ አይሆንም።"

"ሴቶቹ ላይ እያደረስህ ስለ አለኸው የስነ ምግባር ውድቀትስ በነዚህ ልጆች ላይ በአደረግኸው የስነ ምግባር ልቅነት የማትቀጣ ይመስልሃል?" አትኩሮ ተመለከተው።

"ፈቅደው እስከ አደረጉት ድረስ የምጠየቅበት ምንም ነገር አይኖርም። ሴቶቻችሁ ከዚህ በከፋ መልኩ በየደቂቃው ብዙ ድርጊቶችን እንደሚፈጽሙ ማወቅና መረዳት አለብህ።"

ዘሩባቤል መለስ ብሎ አሰበ። በየምሽቱ ከዚህ የባሰ ብዙ ነገር እንዳለ ያ ከውካዋ ወመኔ አሳይቶታል። በዚያ በምሽት ክበብ ያየው ሁሉም ነገር ለመበላሸቱ በቂ ማረጋገጫ ነው ይህንን እንኳን ማስቆም እንዳልቻለ ያውቃል። ማን ነበር የዚች አገር ባለ አደራ? ወጣቱ አልነበረም? ታድያ እሱ ተማርኮ ሱሪውን በሥርዓቱ መልበስ ተስኖት መገጣጠሚያውን ከፍቶ እየሄደ በምን ሞራሉ ነው አገሩን በአደራ ተረክቦ የሚጠብቀው?

"ለማስገደድ ከመሞከሬ በፊት እውነተኛውን ማንነትህንና ወደ ኢትዮጵያ ከገባህበት ቀን ጀምሮ እየሠራህ ያለኸውን ሳትዋሽኝ እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ።" ከፊት ለፊቱ እየተቀመጠ ጠየቀው።

ወፍራም አንገቱን ሲያወዛውዝ ጠቅላላ ሰውነቱ ተንቀሳቀሰ። ምንም የምነግርህ የለም ለማለት እንደሆነ ገብቶታል ለመረጃ መኮንኑ። በአሳየው ትዕቢት ራሱን መቆጣጠር ስለተሳነው እጁ የቻለውን ያህል ከረጅም ፊቱ ላይ ቡጢ አቀመሰው። ግራ አፍንጫው ደም ማመንጨት የጀመረ ቢሆንም የተሰማው አይመስልም።

ቀጥሎ ከነበረው ክፍል የጥይት ተኩስ ተከታትሎ በመሰማቱ የመረጃ መኮንኑ ከሰውየው ላይ የነበረውን ትኩረት አቋርጦ አዳመጠ። አራት ያህል የሽጉጥ ፍንዳታዎች ተሰሙ። ድምጽ እንዳያወጣ አስጠንቅቆት ወደ በሩ ተራመደና ውጭውን ለማየት ሞከረ። በረንዳው ጨለምለም ያለ ስለ ነበር ብዙም አልታይህ አለው። ፊቱን ወደ ውስጥ መልሶ ምርኮኛውን በጥንቃቄ አስተዋለው። ከአፍንጫው እየወረደ ያለውን ደሞ ጎንበስ ብሎ ጭኑ ላይ





እያንጠፈጠፈ ነበር። ገና መጀመሩ ስለ ሆነ ተዘጋጅበት በእርካታ እየወረደ ያለውን ደም ተመለከተ ዘሩባቤል።

"ቀጥሎ ያለው ክፍል ምንድነው?" በቁጣ የተንቀለቀሉ ዓይኖቹን አፈጠጠበትና ጠየቀው።

"ሄደህ ማየት ትችላለህ" አለው እንዳቀረቀረ።

በድጋሚ የተኩስ ድምጽ ሰማ። ከዚያም ከፍተኛ የሆነ የማጓራትና የጠእር ድምጽ ከጆሮው ገባ። የሬዲዮ መገናኛው ከመንጫጫት በቀር አይመልስም። በኃይል ይንጫጫል። ከብዙ ሙከራ በኋላ መልስ መጣለትና መነጋገር ጀመረ።

"ምንድነው ነገሩ? የት ነው ያላችሁት? እየተፈጠረ ያለው አይሰማችሁም እንዴ?" ጠየቀ ረዳቶቹን።

"ችግር የተፈጠረበትን በር እየጠበቅን ነን። ገብተን ምን እንደ ተፈጠረ..." የመረጃ መኮንኑ ጣልቃ ገባ።

"እንደዚያ እንዳታደርጉ። ወደ ውስጥ መግባት የለባችሁም። ወሮ በሉች እርስ በርሳቸው እየተጨራረሱ ሊሆን ይችላል። በሩን ብቻ ጠብቁ" የመረጃ መኮንኑ ሰውየውን በዓይነ ቁራኛ እየተመለከተ አጠር ያለ መመሪያ ሰጣቸው።

"ከሚቀጥለው ክፍል ስለአለው ነገር የማትነግረኝ ከሆነ ስቃይህን አበዛዋለሁ" ቁልቁል ተመለከተው። የመለሰለት የድፍረት ቃል አበሳጭቶታል።

"አንድ ከሃዲ እየቀጠቀጠ መሰለኝ" እረጋ ብሎ መለሰለት።

"የምን ከሃዲ ነው?" ጉንበስ ብሎ አስተዋለው።

"መረጃውን ለእናንተ የሸጠ አቃጣሪ አለ። ዋጋውን ማግኘት አለበት። የሚገባውን እየሰጡት ናቸው።" ወፍራሙ ሰው አንከራፋና በአፋ የተጠራቀመውን ደም ተፋ።

"ማነው መረጃ የሸጠልን?" ሲል ጠየቀው የመረጃ መኮንኑ።

"ከሕዝብ ግንኙነት ባለ ሥልጣኑ ጋር የቀጥታ ግንኙነት የነበረው ሰው ነበር። እሱ ነው ምሥጢራችንን ለመንግሥት ደኅንነት ሠራተኞች የሸጠው" አለው በቁጭት።

"ምንድነው ኢትዮጵያዊ" ሲል ጠየቀው የመረጃ መኮንኑ።

"አበሻን ማመንና መቀበል አስቸጋሪ መሆኑን የተረዳሁት አሁን ነው አለ በልቡ" የረጋው ደም ቁርጥራጭ አፍንጫውን እያነፋነፈው ነበር።

የሚሰማው የጣር ድምጽ እየራቀና እየደከመ ስለነበር የመረጃ መኮንኑ ከተንበረከከበት ተነስቶ ወደ ግድግዳው ተጠግቶ ቆመ። እርስ በራሳቸው እየተጋደሉ ናቸው። የሌባ መጨረሻው ይሄው ነው።

ወደ ሻወር ቤቱ ተራመደና መዝጊያውን ከፈተው። ሦስቱ ሴቶች የሻወር

ቤቱ እርጥብ ሴራሚክ ላይ ኩርችች እንዳሉ ዓይኖቻቸውን እያቁለጨለጨ ተመለከቱት።

"ሲያንሳችሁ ነው።" የእርግማን ናዳ አውርደባቸው መዝጊያውን በኃይል ወርውሮ ጠረቀመውና ወደ ሳሎን ተመለሰ።

ኮቴ ሲተረማመስ ተሰማውና ምርኮኛውን የጎድን እየተመለከተ ወደ በሩ ተራመደና ትክሻውን ዘንበል አድርጎ ውጭውን በስሜት እያሸተተ አዳመጠ። ውጭው ተመልሶ የተለየ የጽልመት ጸጥታ ነግሶበታል። አንገቱን ወደ ውጭው ብቅ አድርጎ በረንዳውን ተመለከተው። ምንም እንቅስቃሴ የለም። ከሌላ ቦታ በመጣው የኤሌክትሪክ ጨረር ሁለቱን የጸጥታ ፖሊሶች በተጠንቀቅ እንደ ቆሙ ከሚቀጥልው በር ላይ ተመለከታቸው።

ውስጥ የተሰማቸው ነገር አለ ማለት ነው። መገናኛውን ሲሞክረው ብዙም ሳያስቸግረው የጸጥታ ፖሊሱ ሬዲዮ ተነሳለት።

"ካላችሁበት ቀጥሎ ያለውን ክፍል ነቅታችሁ ጠብቁ" ትእዛዙን ሲጨርስ ዘጋና ተመለሰ።

ወፍራሙ ሰው ሁለት ቡጢ የቀመሰው ሞላላ ፊቱ አብጦ የዓይኖቹ ቆቦች ወደ ታች መንጠልጠል ጀምረዋል። የረካ መሆኑን ሊያሳየው ፈገግ አለ። "የሚበጅህን አግኝተሃል አስቀያሚ።" አልመለሰለትም ወፍራሙ ሰው።

የብዙ ሰዎች ድምጽ በአንድነት ገብቶ ሬድዮኑ ተንጫጫበት። በአውራ ጣቱ እየነካካ በማስተካከል ድምጾቹን ቀነሰና ተጠባበቀ።

"የመረጃ መኮንን ውኃ ልማት አካባቢ ከአንድ ሕንፃ ውስጥ ነው ያለሁት።"

"ምን ልርዳህ ምንድነው የፈለግኸው ዝግጁ ነኝ" ከወዲያኛው መስመር የነበረው ወፍራም ድምጽ ለእርዳታ ዝግጁ መሆኑን ገልጾለት።

"ኃይል ያስፈልገኛል። የሕንፃው እያንዳንዱ ክፍል መፈተሽ አለበት። መኪናም ያስፈልገኛል። የተያዙ እስረኞች አሉ።"

"እሺ አደርጋለሁ" ከወዲያኛው ጫፍ የነበረው ድምጽ ተቋረጠና የመገናኛ ሬዲዮኑን ወደ ኪሱ መለሰው።

ከግማሽ ሰዓት ቆይታ በኋላ በሕንፃው ግቢ ሁለት የጭነት መኪናዎች ደረሱ። በደቂቃዎች ልዩነት ሁሉም ነገር የገበያ ሽብር እስኪመስል ድረስ ትርምስምሱ ስለ ወጣ አንደኛው የሌላውን የሬዲዩ መስመር እጨናነቀውና የጦር ሜዳ አስመሰለው።

የመረጃ መኮንኑ ሰውየውንና ሦስቱን ሴቶች አዲስ ለመጡት ፖሊሶች አስረክቦ ወደ ሁለቱ ፖሊሶች ሄደና የተዘጋውን በር አንኳኳው። ጸጥታ ብቻ ነው። ደገመና አንኳኳው። መልስ አልነበረም።

ለሦስተኛ ጊዜ ደበደበው። የታፈነ የማንቋረር ድምጽ የሰማ መሰለው። ነፍሱ አልወጣችም ማለት ነው ሲል አሰበ። በመሞት ላይ ያለ የጠእር





ድምጽ እንደ ሆነ ገመተ። ጉዳት የደረሰበት ሰው ለመሞት ከጠእር ጋር እየታገለ ነው።

እጀታውን ጨብጦ ወደ ጎን ሲጠመዝዘው ቋ ብሎ ተከፈተና ትንሽ ያህል ሄዶ ቆመ መዝጊያው በቁልፍ አልተዘጋም ነበር። እንደማይከፈት ተረዳ። የፖሊሱን ትክሻ ነካ አደረገና ወደ ውስጥ እንዳይገባ ምልክት ሰጠው። በሩን የወጠረው የሰው ትክሻ ሊሆን እንደሚችል ጠርጥሯል።

"በሩን የያዘው ወለሉ ላይ የተጋደመው ነገር ነው። እያንቋረረ ያለው ሰው መሆን አለበት።" ፖሊሱ በሹክሹክታ ለዘሩባቤል ሊያስረዳው ሞከረ።

"ከትንሽ ደቂቃዎች በፊት ድምጽ ሰምተን ነበር"ሲል ሁለተኛው ፖሊስ ለመረጃ መኮንኑ ነገረው።

"በኃይል መግፋት ሊኖርብን ነው።" ቀጭኑ ፖሊስ ፊቱን መልሶ ተናገረ።

"ከውስጥ ያለው ሰው ሊተኩስና ሊመታህ ይችላል።"

"እንደዚያ ከሆነ በርግጥ ያስቸግራል" አለ ቀጭኑ ፖሊስ፡

"ሌላ አማራጭ የለንም።"

"አይመስለኝም" አለ የጸጥታ ፖሊሱ "በሩ የተያዘው ከስር በኩል ስለሆነ ከበሩ ስር የወደቀ ነገር ያለ ይመስለኛል።"

ጎንበስ ብሎ የበሩን ስር ለማየት ሲሞክር የጠቆረና የረጋ ደም ወደ ውጭ እየተገፋ ሲመጣ ተመለከተ።

የረጋው ደም ወደ ውጭ እየተገፋ የበለጠ መፍሰስ ጀመረ። የማንቋረሩ ድምጽ ድጋሜ ተሰማና ከበሩ ስር የወደቀው ሰው መወራጨት ቀጠለ። ነፍሱ ከሥጋው ልትለይ እየታገለችው መሆን አለበት ሲሉ አሰቡ ሦስቱ ሰዎች። ከሞት ጋር ትግል የገጠመ ሰው ነው በሩን የያዘው። በተወራጨ ቁጥር ወደ ውስጥ እየራቀ በሩ እየተከፈተ ነው። እየተፈራገጠ ወደ ወለሉ መሀል ሲርቅ በሩን እየለቀቀው በመጠኑ ተከፈተ።

"እጅህን ስጥ። ተከብበሃል..." ቀጭኑ የጸጥታ ፖሊስ እየደጋገመ ቢጮህም ከገደል ማሚቶ በስተቀር ከውስጥ የሚመጣ ድምጽ አልነበረም። ከበሩ ስር የወደቀው ሰው ከሞት ጋር ይታገላል።

የረጋው ደም ወደ ውጭ በብዛት እየመጣ ነው። ሰውየው በተወራጨ ቁጥር ወደ ውስጥ እየራቀ በሩም በዚያው መጠን እየተከፈተ ነው።

ያለ የሌለ ኃይሉን ጨምቆ የመጨረሻ ሙከራውን አድርጐ ለመነሳት ሲሞክር ሳይሆን አይቀርም ገርበብ ያለውን በር በእግሩ ሲገፈትረው መልሶ ተዘጋ። የመረጃ መኮንኑ ሁለቱን ፖሊሶች ግራ በመጋባት ሲመለከታቸው እነሱም ተመለከቱት። ሰውየውን በጥይት የደበደቡት ሰዎች ወዴት ገቡ? በግንባሩ ምልክት እረዳቶቹን ሊጠይቃቸው ሞከረ። አልተግባቡም። የፍርሃት በርኖሱን አሽቀንጥሮ ጥሎ ቀጭኑ ፖሊስ ወደ ክፍሉ ገባ። ከሞት ጋር ይታገል የነበረው ሰው በደም እንደተነከረ

ተዘርግቷል። መወራጨቱን ያቆመ ቢሆንም ነፍሱ ገና አልወጣችም። የረጋው ደም በምንጣፉ ላይ አልፎ አልፎ የጉበት ምታሪ መስሎ እየተጉማመደ ረግቶ ይታያል።

በጥይት የተደበደበው ሰው የመጨረሻ እስትንፋሱን ሳይጨርስ ትንሽ ቢጠብቀው ወደደ። ነፍሱ ባትወጣም ለመናገር አይችልም። አይኖቹ ከመጠን በላይ ወደ ውጭ ፈጠዋል። በክፍሉ የወረደው ደም ደስ የማይል ሽታ ይተነፍጋል። ደም ያልነካውን ምንጣፍ እየመረጠ ወደ ወደቀው ሰው ተራመደና በርከክ ብሎ እስትፋሱን አዳመጠ። ከልቡ አካባቢ የሚኩረፈረፍ ድምጽ ቢኖርም ተስፋ አልነበረውም። ዘሩባቤል ተበሳጨ። ዘግይቷል።

ቀለሆቹን ለቀመና ከጃኬቱ ኪስ ጨመራቸው። የወደቀው ሰው።

አገሩን ከዷል የሰውን ሀብትና ንብረት ዘርፏል። ሕዝብን አሸብሯል። ሩጫውንም ጨርሷል። የሕይወቱ የመጨረሻው እድገቷ በዚህ መልኩ ተጠናቅቋል። የማይጠቅም ገልቱ። በፌደራል ፖሊስ የጸጥታ ሠራተኛ ነበር።

ወደ ሻወር ቤቱ የገባው ፖሊስ ምንም ያገኘው ነገር ስላልነበር የመገረም ምልክት እየታየበት ተመለሰ። ሰውየውን ያቆሰሉት ሰዎች መንፈስ መሆን አለባቸው። የመረጃ መኮንኑ ፖሊሱን ግራ የተጋባ በሚመስል ስሜት ቀና ብሎ አስተዋለው።

"ምንም ነገር የለም?" ጠየቀው ፖሊሱን።

"ምንም የለም" አንገቱን እየነቀነቀ መለሰለት የጸጥታ ፖሊሱ።

"ከውስጥ የነበሩት ሰዎች በየት ወጡ?"

ከመመለሱ በፊት የጸጥታ ፖሊሱ እራሱን እያሻሸ ለማሰብ ሞከረ። የት ደረሱ ይሆን በየት በኩል ወጡ? ግራ ያጋባል።

"እራሱን በራሱ አጥፍቷል እንዳንል በእጁ ላይ የተገኘ መሣሪያ የለም" አለ ዘሩባቤል።

"በጥይት ከመመታቱ በፊትም ሆነ ከተመታ በኋላ የሌሎች ሰዎችን ትግልና ድምጽ በክፍሉ ውስጥ እሰማ ነበር" አለ የጸጥታ ፖሊሱ።

"የሌሎች ሰዎች ንትርክ እንደ ነበር ለኔም ተሰምቶኛል" የነበረውን ሁሉ ለማስታወስ ሞከረ የመረጃ መኮንኑ።

"በተዓምር ተሰውረዋል ማለት ነው" አለ ፖሊሱ።

"የመታጠቢያው ክፍል በጥንቃቄ መታየት ያለበት ይመስለኛል" የመረጃ መኮንኑ ወደ ሻወር ቤቱ ገብቶ በአልሙኒየም ፍሬም የተገጠሙትን የመስታወት መስኮቶች፣ የመታጠቢያ ገንዳውን የመጸዳጃ ሳህኑን ጭምር በጥንቃቄ መመርመር ጀመረ። የሚገርም ነገር ነው ምንም ነገር የለም።

መስኮቶቹ ከውስጥ ከመቆለፋቸውም በላይ ምንም የእጅ አሻራ ሳያርፍባቸው በተዘጉበት እንዳሉ እርግጠኛ ነበር። ወደ ፖሊሱ ተመለሰ። አስገራሚ ጉዳይ ነው።

"እንደተዘጉ ናቸው። በገመድ ካልተጠቀሙ በስተቀር ማንኛውም





ሰው ከአራተኛ ፎቅ ዘሎ ይወርዳል ብሎ ለመገመት የማይታመን ጉዳይ ነው።" አለው በረጅሙ እየተፌነሰ ፖሊሱ።

"የሻወር ቤቱን በደንብ ለማየት ሞክሬ ነበር።" አለ የመረጃ መኮንኑ "የወደቀውን ሰው አይተኸዋል?" ሲል ጠየቀው። ራሱን በአሉታ አወዛወዘ። "ምነው ጠየቅኸኝ ታውቀዋለህ እንዴ?"

"የፌደራል ፖሊስ የጸጥታ ሠራተኛ ነው።"

"እንዴት ሊሆን ይችላል?" አለው ግራ እየተጋባ።

"ሆኗል" አለውና በረጅሙ ተነፈሰ። የጸጥታ ፖሊሱ ማረጋገጥ ስለፈለገ ጉንበስ ብሎ ተመለከተው።

"የሻወር ቤቱን ሳህን አንስተን ማየት ይኖርብናል። ምናልባትም ወደታችኛው ክፍል ሊያወርድ የሚችል ጠባብ ቀዳዳ ሊኖር ይችላል።" አለው።

የሽንት ቤት ሳህኑን ለማንሳት ቢሞክሩት ስለጠበቀባቸው መታገሉን ተውትና የገላ መታጠቢያውን ሳህን ሞከሩ። በቀላሉ የሚነሳ አልነበረም። ከኮንክሪቱ ጋር በሲሚንቶ ተለስኖ ነው የተሠራው የብርሃን መግቢያ መስኮትም በፍርግርግ ብረት የተገጠመ ስለሆነ ሰው አይደለም የድመት ግልገል እንኳን ሊያሳልፍ የሚችል አልነበረም።

የመረጃ መኮንኑ በነጭ ሴራሚክስ የተገነባውን ግድግዳ በጥንቃቄ መመርመሩን ቀጠለ። በቅሎ ጠፍቶት ኮርቻውን እንደ ፈተሸ ሰው ዓይነት።

የመታጠቢያ ገንዳውን ጭምር በእጁ እየዳሰሰና እየነካካ በጥንቃቄ ተመለከተው። ከተነጠፈው ሴራሚክስ ጋር ጥርስ በጥርስ ተያይዟል።

"አብሮ የተገነባ ነው።" አለ ለራሱ በርግጥም በትክክል ሁሉም ነገር ደረጃ ጠብቆ የተሠራ ነበር። እራሱን ጠየቀ መንፈስ ይሆኑ እንዴ? እየተዟዟረ ጠባቡን ክፍል ተመለከተው። መልስ የማይሰጥ ግኡዝ ነገር ነበር ጠባቡን ክፍል የያዘው።

"ሰዎቹ መንፈስ መሆን አለባቸው" ወደ ፖሊሱ ቀና ብሎ ተናገረ የመረጃ መኮንኑ ዘሩባቤል።

"ምን አልከኝ?" የጸጥታ ፖሊሱ። ጠየቀው።

"ሰዎቹ መንፈስ መሆን አለባቸው እያልኩ በማሰብ ላይ ነበርሁ" ክት ብሎ ቢስቅ በተደሰተ ነበር የጸጥታ ፖሊሱ ግን አላደረገም።

"እኔም እንደሱ በማሰብ ላይ ነበርሁ" አለ የጸጥታ ፖሊሱ።

ከተንበረከከበት ተነስቶ ሲቆም የጸጥታ ፖሊሱ ጎንበስ አለ። የሻወር ገንዳውና ወለሉ ተመሳሳይ ነው። የግድግዳውን ጠርዝ ለረጅም ደቂቃ መረመረው። ምንም ምልክት የለም።

"ምንድነው ነገሩ?" የመረጃ መኮንኑን ግራ በመጋባት ተመለከተው።

ትክሻውን ከፍ አድርጎ አንቀሳቀሰና "አልገባኝም…።" ሲል መለሰለት። በርግጥም የሚገባ አልነበረም። ሰውን ያህል ነገር የት ደረሰ ተብሎ

ይታሰባል? ከአራተኛ ፎቅ በርሮ ወዴት መሰወር ይችላል::

"ሁኔታው ግልጽ አይደለም:: የተገኘ ቀዳዳ ከሌለ ምርምራችን የተወሳሰበ ይመስለኛል" የጸጥታ ፖሊሱ ከተንበረከከበት እየተነሳ ተስፋ በመቁረጥ ተናገረ::

የመረጃ መኮንኑ እራሱን በዝግታ አወዛወዘና የሻወር ቤቱን ዙሪያ በድጋሚ በጥንቃቄ መፈተሽ ያዘ:: መልስ ያልተገኘላቸው ብዙ ጥያቄዎች እየመጡ መሆናቸው እልህ ውስጥ እየከተተው ነው:: ከትንሽ ጊዜ በፊት በርከት ያሉ ሰዎች በዚህ ክፍል ውስጥ ነበሩ:: የተከፈተ ወይም የተቀደደ ነገር ከሌለ እንዴትና በየት ወጥተው ሄዱ? መንፈሱ እንደተወጠረ ወደ ሻወር ቤቱ ተመልሶ ገባ:: አእምሮው የሆነ ነገር እያጫረበት ነው:: በአንደኛው መአዘን በኩል የተሠራው ሴራሚክ ክፍተት እንዳለው ተመለከተ:: አንድ ሜትር ቁመትና ከሰባ ሳንቲ ሜትር ስፋት የማይበልጥ እስከ ወለሉ ድረስ ከሌላው ሴራሚክ የተለየ ቀጭን ክፍተት አለው:: ይህ ቦታ አእምሮውን አስጨንቆ ለያዘው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል ሲል አሰበ:: እንደ ጭራ የቀጠነውን ክፍተት ወደ ኋላው ራቅ አለና በጣቱ ጠቆመ::

"ያንን ቦታ" ወደ ጸጥታ ፖሊሱ ፊቱን በግማሽ እንደ መለሰ ሊያሳየው ሞከረ::

"እየሁት..." አለ የጸጥታ ፖሊሱ::

የመረጃ መኮንኑ ግድግዳውን በጣቶቹ መታ መታ አደረገ:: ድምጹ ከሌላው የተለየ ነበር:: ጣቶቹን አጥፎ በኩርኩሙ በኩል አመም አድርጎ መታው::

"ደባል እንደ ሆነ ያስታውቃል:: ሹል ብረት እናገኛለን" የጸጥታ ፖሊሱ በጃኬቱ የውስጥ ኪስ ይዞት የነበረውን ጩቤ አውጥቶ ሊፈለቅቀው ሲሞክር የሳንጃው ጫፍ ተጣመመ::

እየደጋገመ ቢሞክረውም ጩቤውን ከማጣመም በቀር ጩቤው መግባት አልቻለም:: ፍንጩ ግን ተገኝቷል:: ሲል እያሰበ ቀና አለ:: ሰዎቹ የወጡት በዚህ በኩል ነው የሚሆነው::

ጩቤውን ወደ መሃደሩ መለሰና ዓይኖቹን አቅርቦ ሴራሚኩን ተመለከተው:: ከወዳኛው በኩል መጠነኛ ደብዛዛ ብርሃን የሰጠው መሰለው:: እየደጋገመ ከተመለከተው በኋላ ወደ መረጃ መኮንኑ ቀና ብሎ ተናገረ::

"ይህ ነገር በር ይመስለኛል:: መጠነኛ ብርሃን እንደሚያሳይ እገምታለሁ::"

የመረጃ መኮንኑ ጉንበስ አለና እንደ ጸጥታ ፖሊሱ አሻግሮ ለመመልከት ሞከረ::

"ምንም ብርሃን የሚሰጥ ነገር የለም:: አእምሮህ የፈጠረው የብርሃን ውጋገን ነው::" በተስፋ መቁረጥ ተነፈሰ:: የመረጃ መኮንኑ::





"እርግጠኛ ነኝ ሰዎቹ የወጡት በዚህ በኩል ነው:: ያልገባኝ በምንና እንዴት ተከፍቶ እንደሚዘጋ ብቻ ነው::" አለ የጸጥታ ፖሊሱ::

የመረጃ መኮንኑ ባለመስማማት ትክሻውን ወደ ላይ ሰበቀና ተመለከተው የፀጥታ ፖሊሱን::

የጸጥታ ፖሊሱ ሴራሚክሱን አንድ ጊዜ በጫማው ሲመታው መልሶ አነጠረው:: ከፍ ብሎ በሰው ቁመት ልክ ከግድግዳው ላይ የተገጠመ የመጥሪያ ደወል ተመለከተ የሁለት ክብሪት ቀፎ ያህል መጠን ያለው ነው ተንጠራርቶ ሲጫነው በመደወል ፋንታ አረንጓዴ ብርሃን ሰጠው:: ቢጫው ብልጭ አለና ቀዩ ሲበራ ሴራሚኩ እየተንሸራተተ ወደ ግድግዳው መግባት ሲጀምር ሲታገለው የነበረው ስፍራ በር ሆነና ተከፈተ::

የመረጃ መኮንኑ ሬድዮኑን ሲከፍት የአንድ ሰው ድምጽ ገባለት:: ከአዲስ አበባ የጸጥታ ፖሊስ ዋና አዛዥ ነበር የተደወለለት::

"የምረዳህ ካለ በአጭሩ አስረዳኝ" አለው የደወለው ሰው::

"የአንተ የቅርብ ሠራተኛ ተገድሎ ከዚህ ወድቆ አግኝተነዋል" የመረጃ መኮንኑ ወደ ወደቀው ሰው እየተመለከተ ተናገረ::

"ማነው የኔ የቅርብ ሠራተኛ?" ግራ የገባው መሰለ::

ስሙን ሲነግረው በድንጋጤ እናቱ የተከፈለ ያህል ተሰማውና ከንፈሩ መድረቅ ጀመረ::

"እንዴት ሊሆን ይችላል" አለ ኃላፊው "በእረፍት ላይ ስለሆነ አሁን የሚገኘው በናይሮቢ ኬንያ ነው::"

"መቼ ነበር ወደ ኬንያ የበረረው::" የመረጃ መኮንኑ ጠየቀው::

የጸጥታ ፖሊስ ኃላፊው ትንሽ አሰበ:: ቀኑን በትክክል ማስታወስ አይችልም::

"ከአሥራ አምስት ቀን በፊት ይመስለኛል::"

"ተመልሶ መጥቷል ማለት ነው:: አየር መንገድ ደውለህ መቼ እንደገባ ልታረጋግጥ ትችላለህ::"

"እርግጠኛ ነኝ እያልከኝ ነው" ጠየቀ የጸጥታ ፖሊስ ተጠሪው::

"ከእርግጠኛም በላይ እርግጠኛ ሆኜ ነው የምነግርህ:: ሰውየው ከዚህ ወድቋል::"

"እንዴት ሊሆን ይችላል? በምንስ ምክንያት?" ኃላፊው ግራ የተጋባ መሰለ::

"እሱን ወደፊት የምንመለከተው ጉዳይ ይሆናል:: የደወልኩልህ ይህንን ልነግርህ ሳይሆን የሕንፃውን ክፍሎች ለመፈተሽ ችግር ስለ ገጠመን ነው:: የክፍሎቹ በሮች ከውስጥ የተቆለፉ በመሆናቸው መግባት አልቻልንም::

ክፍሎቹ በውስጥ በኩል ተቆላልፈው አንደኛውን ከሌላቸው የሚያገናኝ የአደጋ ጊዜ መተላለፊያ በር አለ:: ወንጀለኞቹ በነዚህ በሮች እየተሽሎከለኩ ከአንደኛው ክፍል ስንደርስባቸው ወደ ሌላው እያፈገፈጉ ናቸው::

ቀጥሎ አለው ክፍል ውስጥም ቆስለው የወደቁ ሰዎች ይታዩናል::" የመረጃ መኮንኑ ጥያቄ ሳይሆን ቀጥታ ትእዛዝ ነበር የሰጠው::

"ሌሎችም የተገደሉ ሰዎች?" የመምሪያ ኃላፊው ጠየቀው::

"ሌሎች የተገደሉ ሰዎች ከወለሉ ላይ ወድቀው ይታየኛል:: ምሥጢራቸውን ለመደበቅ ሰዎችን እያስወገዱ መሆናቸውን ነው የተገነዘብኩት::"

"ውጭውን አላስከበብክም እንዴ?" የጸጥታ ኃላፊው ኮስተር አለ::

"የሕንፃው ዙርያ እየተጠበቀ ነው:: ያም ሆኖ በቂ ሰው የለንም::"

ይህንን በሚነጋገርበት ሰዓት በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ እንደ ቆመ ሌላ በር በዓይኑ እየፈለገ ነበር:: የፀጥታ ፖሊሱ ቀድሞት የምሥጢር በሩን አግኝቶት ሲመለከት ደስ አለው::

"የሕንፃው ግራውንድ ከወንዝ ጋር ሊያገናኝ የሚችል መንገድ ይኖራል የሚል ስጋት አለኝ::" የመረጃ መኮንኑ ጥርጣሬውን ገለጸለት::

"እንደዚያ ከሆነ በጣም ዘግይተሀ ነው የነገርከኝ:: ወደ ሕንፃው ከገባችሁ ከአንድ ሰዓት በላይ ሆኗችኋል:: የምትለውን አይነት መንገድ ከተጠቀሙ የምትጠብቁት ባዶ ቤት ነው ማለት ነው" የጸጥታ ኃላፊው አነጋገር ፌዝ የተቀላቀለበት ነበር::

መደዳውን ያሉትን ክፍሎች እየፈተሸ ከመጨረሻው ክፍል ደረሰ:: በዚህ ክፍል ያለው ለየት ያለ ነገር ነበር:: በኮንክሪት የተሠራ ሜትር በሜትር ስፋት ያለው ክፍት ቦታ የበርሜል ቅርጽ እንደ ያዘ ይታያል:: አዘቅዝቆ ተመለከተው:: ቀዳዳው ከክፍሉ ግድግዳ ጋር ተጠግቶ የተሠራ ነበር የሚቀጥለውን ክፍል ተመለከተው በጥቁር ጨለማ ተሞልቶ እንደ ጥልቅ ውቅያኖስ ያስፈራል:: የፈለገው ይሁን ብሎ በመሰላሉ ወረደ:: የጸጥታ ፖሊሱም ተከተለው::

ወንበሮችና አራት ያህል የተለያዩ መጠን ያላቸው ጠረጴዛዎች ተራርቀው ተቀምጠዋል:: የመጨረሻዎቹ ክፍሎች እስከ ግራውንዱ ድረስ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውና ንጽኅናቸውን ያልጠበቁ ናቸው:: በአደጋ ጊዜ መውረጃ መሰላል የተገጠመላቸው ስለሆኑ ከመጨረሻው አራተኛ ፎቅ እስከ ግራውንድ ያለው ክፍል በሙሉ በተመሳሳይ ይዘትና መጠን የተዘጋጀና በትርክም ክም ዕቃ የተሞላ ነበር:: አልባሌ ለማስመሰልም በየመውረጃ ጉድጓዶቹ አፍ ላይ አልባሌ ዕቃ ይጣልባቸዋል:: ሁለቱን የጸጥታ ፖሊሶች እንዳስከተለ መሰላሉን በጥንቃቄ እየረገጠ ከሦስተኛው ክፍል ሲደርሱ ከላይኛዎቹ ክፍሎች የተለየ ነገር ገጠማቸው::

እርስ በርስ በተጠላለፉ ቀጫጭን የኤሌክትሪክ ሽቦዎችና ኬብሎች የሳተላይት ስልኮች ጥሪ መቀበያና ማስተላለፊያ የስልክ ቀፎዎች ጠረጴዛዎችና የመቀመጫ ወንበሮች የፋይል ማስቀመጫ ሳጥኖች ጢም





ብሏል:: የፎቶ ኮፒ፣ የፕሪንተርና የፋክስ ማሽኖቹም በኬብል እንደ ተገናኙ ናቸው::

በረቀቀ የቴክኖሎጂ ውጤት የተሞላው ክፍል ከሁሉም ክፍሎች ስፋት ያለው ነው:: ከላይ ወደ ታች ከሦስተኛው ፎቅ ላይ ደርሰዋል:: እስከ ግራውንዱ አራት ፎቅ ይቀራቸዋል:: የሚቀጥሉት ክፍሎች ምን እንደያዙና እንደሚገጥማቸው የሚያውቁት ነገር የለም:: የተደበላለቀ ጦርነት ሊከሰት የማይችልበት ምክንያት የለም:: የሚመለከቷቸው የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች ከነጥቅምና ጉዳታቸው ለይቶ በመረዳት መፈተሽ የሚችል ባለሙያ ያስፈልጋቸዋል:: እንደዚያ ካልሆነ ጉዳት እንደሚያደርሱ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው:: ምናልባትም አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር ተጠምዶባቸው ሊሆን ይችላል:: በጥርጣሬና በስጋት ይመለከቷቸው ጀመር:: የመረጃ ሰዎች እንደ መሆናቸው ከመቅመስ በፊት ማሽተት ለመርዝ ፍቱን ማርከሻ መሆኑን ያውቃሉ::

በቴክኖሎጂ የተራቀቁ ስልጡን ወሮ በላዎች ይህንን ከማድረግ አይመለሱም ሲል አሰበ የመረጃ መኮንኑ:: ከኤሌክትክ ጋር የተቆራኙ ዕቃዎች መነካት የለባቸውም:: መጥፎ መጥፎ ነገሮችን እያሰበ በሽቦ የተጠላለፉትን የኮምፒውተር ዕቃዎች እንደተጠመደ ፈንጅ በጥርጣሬ እየደጋገመ ተመለከታቸው:: እሱ ብቻ ሳይሆን ረዳቶቹም በተመሳሳይ ስሜት ውስጥ ነበሩ::

"አስጊ ነገር የያዘ ይመስላል?" አለ ፖሊሱ::

የመረጃ መኮንኑ በአዎንታ እራሱን አነቃነቀ:: "ትክክል ነህ" የፈንጅ መመርመሪያ መሣርያ ያስፈልገናል" ሲል መለሰ::

መደረግ ያለበት ይህ ብቻ ነው:: የሚከተለው ይከፋና ሁሉም ነገር ያከትማል:: ሕንፃው ወደ ፍርስራሽነት ይቀየርና ቁርጥራጭ የሰዎች ሥጋ በውስጡ ይቀብረዋል:: "በቢላዋ ቀልድ የለም እለች ዶሮ" አሉ ጋሼ እንትና ፈገግ አለ የመረጃ መኮንኑ::

"አሁኑኑ መድረስ አለባችሁ መያዝ ያለባችሁን መሣሪያዎች እንዳትረሱ::" ሬዲዮኑን እየዘጋ የፈንጅ ባለሙያዎችን ጠርቻለሁ" አለ ፖሊሶቹን እየተመለከታቸው::

የፈንጅ ባለሙያዎቹ የወሰደባቸው ጊዜ ከግማሽ ሰዓት አይበልጥም:: ግቢው በደኅንነት ፖሊሶች እየተበረበረ ስለነበር ፈታሾችን እያለፉና እየገፈታተሩ ሲጣደፉ በስፍራው የነበረው ሁሉ ፈንጅ አምካኝ ባለሙያዎቹን ሲመለከት በስጋት መንሾካሾክ ጀመረ::

ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ ከተመለከቱ በኋላ መሣሪያቸውን አውጥተው ወደ ፊት በመዘርጋት በክፍሉ ወለል ላይ እየገፉ መመርመራቸውን ቀጠሉ:: ወለሉንና ግድግዳውን በጥንቃቄ እያሰሱ ወደ ኮምፒውተሮቹ ሲጠጉ መርማሪዎቹ ኤሌክትሪኩን አንዱ፣ ከሌላው ለይቶ ለመስማት አስቸጋሪ

የሆነ ድምጽ ጠባቡን ክፍል በጠበጠው:: ለተወሰነ ጊዜ በስጋት ቢዋጡም ሰላም ሆነ::

"ከአደጋ ነገር ነጻ ናቸው" የፈንጅ ባለ ሙያው ሲናገር የመረጃ መኮንኑ በእፎይታ ተነፈሰ::

"ዋና ዋና የሆኑትን ነገሮች..." በጆርባው በኩል እንደ ቆመ እንዲፈጥን አዘዘው ::

የፋይል ማስቀመጫዎቹ የተለያዩ የኮድ ጽሑፎች የያዙ በመሆናቸው ጊዜ ወስዶ መመርመርን የሚጠይቅ ነበር:: ዳታዎች በየራሳቸው መስመር ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ኢንተርኔቶች የተገጠሙ በመሆናቸው በዚያ ደቂቃ ለማየት የማይሞከር ነው:: የኮምፒውተር ባለ ሙያው ምን ማድረግ እንዳለበት አሰበ::

"ዋና ዋና የሚል ነገር የለም ጌታዬ:: እያንዳንዱን ፋይል እየከፈትን ማየት ይጠበቅብናል:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ ብዙ ጊዜን የሚፈጅ ነው:: ኮምፒውተሮቹ በፋይል የተጨናነቁ ይመስለኛል..." ንግግሩን አቋርጦ አመነታ::

"ኢንተርኔት ውስጥ ግባና..." የመረጃ መኮንኑ አመልካች ጣቱን ወደ ስክሪኑ ሲጠቁም የኮምፒውተር ባለ ሙያው አቋረጠው::

"በዛሬው ቀን ብቻ ብዙ አለም አቀፍ መልእክቶችን አስተናግዷል::"

ለግማሽ ሰዓት ያህል መታገስ ነበረበት የመረጃ መኮንኑ:: በተወሳሰበ ምሥጢር የታሰረ በመሆኑ በፍጥነት መልስ ማግኘት እንደማይቻል ተረዳው:: መታገስና መጠበቅ ነው ያለበት:: የረቀቀውን ቴክኖሎጂ በጥድፊያ መልስ እንዲሰጥ መሞከር ከምኝነት በዘለለ ጥቅም ሊያስገኝ አይችልም::

እንደ ሕፃን ዓይኑን እያንከራተተ የሚያደርጉትን ለተወሰነ ጊዜ ተመለከተ::

"ወደ ቢሮ ተወስዶ መታየት ይኖርበታል" አለ ባለ ሙያው::

በመስማማት ራሱን ነቀነቀ የመረጃ መኮንኑ::





# ምእራፍ ሀያ ሰባት

ከቴሌ ውጭ ዓለም አቀፍ ጥሪ የሚያደርገውን የስልክ መስመር ያገኘው በስንት ትግል ነበር:: ይህ መስመር በአገር ውስጥ ካለው የስልክ መስመር ሳይገናኝ ወደ ተፈለገበት አገር መልእክትን ያስተላልፋል ጥሪዎችንም ይቀበላል::

መስመሩ ምሥጢራዊ መልእክትን ለማስተላለፍ ከመጥቀሙ ሌላም ቴሌ ከሚያስከፍለው ያልተመጣጠነ ክፍያ ነጻ ያደርጋል:: አብዛኛው ሰው የዚህ ሕገ ወጥ የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆኑ ወደ ውጭ አገር ከሚደረጉ ጥሪዎች ቴሌ ዘጠና ፐርሰንት ገቢውን አጥቷል ተብሎ ይታመናል:: ከጥቅሙ በተጨማሪም የሀገርን ደኅንነት ለመጠበቅ ሲባል ክትትል ሊደረግባቸው የሚችሉ መረጃዎችንም አጥቷል:: እነዚህን ድክመቶች እያሰበ ወደ ኮምፒውተር ባለ ሙያው ተመለከተ የመረጃ መኮንኑ::

"ሁሉም ኮምፒውተሮች በጥንቃቄ ተጭነው ይሂዱና ከኔ ቢሮ ውስጥ ገብተው ይቆለፍባቸው:: አንተ እራስህ ከዚያ ሳትለይ በውስጣቸው ያሉትን መረጃዎች እንድትፈትሻቸው አደራ" የጸጥታ ፖሊሱንና የኮምፒውተር ባለሙያውን ተራ በተራ ተመለከታቸው ዘሩባቤል::

የተዘረጋጉትን ገመዶች እያላቀቁ መሰብሰባቸውን ከአረጋገጠ በኃላ ከሚቀጥለው ፎቅ ወርዶ እያንዳንዱን ነገር በጥንቃቄ ተመለከተ:: በክፍሉ የተተረካከሙ ዕቃዎች ታጅበውበታል:: የጸጥታ ፖሊሱ አንዳንዶቹን ዕቃዎች ገልበጥ እያደረገ ተመለከታቸው:: ብዙም ጥቅም የሚሰጡ አይመስልም::

የመጨረሻ ምድር ቤት ሲደርሱ ክፍሉ በጨለማ የተዋጠ ነበር:: ቀዝቃዛማው በጥቁር ጨለማ የተዋጠው ክፍል ቀደም ሲል ከአያቸው ክፍሎች በሦስት እጥፍ የሚበልጥ ስፋት ያለውና በእርጥበት የከበደ ነው:: ከመቃብር የከበደ አስፈሪነት ያለው ግራውንድ ይቀዘቅዛል የሚለው ቃል አይገልጸውም::

የመረጃ መኮንኑ የባትሪዋን ቀጭን ብርሃን እንደ ነብር ጅራት እያወናጨፈ በግድግዳው ላይ ማብሪያና ማጥፊያ ፈለገ:: በአንደኛው መአዘን ግድግዳ ላይ የተለጠፈ ማብርያና ማጥፊያ ቢኖርም የሚሠራ አልነበረም:: ወደ ጣሪያው በማቅናት አምፑል መኖር አለመኖሩን መፈተሽ ጀመረ:: መሃል አካባቢ አቃፊ ቢንጠለጠልም አምፑል ግን አልነበረውም:: ክፍሉ ከመቀዝቀዝም መጥፎ ጠረን እንደ አክስጂን የሚረጭ ነበር::

አንደኛውን ከሌላው የምታገናኘው ቀዳዳ ከላይ እስከ ታች ድረስ የመጣችው በተመሳሳይ አቅጣጫ የውኃ ልኳን ጠብቃ ቢሆንም መጨረሻው ግራውንድ ስትደርስ አላገኟትም::

ከፊት ለፊቱ የመብራት መቆጣጠሪያ የሚመስለው መሣሪያም በእንግሊዝኛ የተጻፈ ማስጠንቀቂያ ተለጥፎበታል።

"መንካት ፈጽሞ ዩተከለከለ ነው።" የሚለው ጽሑፍ ቀስቱ ወደ በተኖቹ የሚያመለክት ነበር። የመጣውን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ አለ ለራሱ።

"አንድ ፍንጭ ያገኘሁ ይመስለኛል" ከኋላው ወደ ቆመው ፖሊስ ፊቱን መልሶ ተናገረ ዘሩባቤል።

"ምንድነው" ትዕግሥት በማጣት ጠየቀው የጸጥታ ፖሊሱ።

"ይህ መቆጣጠሪያ የተገጠመው መብራት ለመቆጣጠር ታስቦ አይመስለኝም" የመረጃ መኮንኑ በጥርሶቹ መካከል ተናገረ።

"አልገባኝም" አለ ፖሊሱ "እና ታዲያ ለምን አገልግሎት..." ነው።

"ወደታችኛው ክፍል ለመውረድ የሚጠቀሙበት መሣሪያ ሳይሆን አይቀርም። በመረጃዬ ላይ ስለዚህ መሣሪያ ተጠቁሞኝ ነበር።"

"እንዴት ተደርጎ?" ፖሊሱ ጠየቀው።

"ወደ መጨረሻው ግራውንድ የሚወርዱበት በኤሌክትሪክ የተገጠመ ሊፍት እንዳላቸው ተነግሮኛል" የመረጃ መኮንኑ ትክሻውን ሰበቅ አድርጎ ፖሊሱን ተመከተው።

"እርግጠኛ ነህ" አለና ትኩር ብሎ ተመለከተው።

"የመውረጃ መሰላሉ ከላይ መጥቶ የቆመው ከዚህ ክፍል ውስጥ ሲደርስ ነው። እንደምትመለከተው ክፍት መስኮትም ሆነ በር የለውም። ከላይ የመጡት ሰዎች በነዚህ መሣሪያዎች ተጠቅመው ወደ ግራውንዱ ካልገቡ በስተቀር ወዴት ሄዱ ተብሎ ይታመናል?" ፖሊሱን እየተመለከተ መለሰለት።

"ሁሉም ነገር ግራ አጋቢ ነው" አለ የጸጥታ ፖሊሱ።

"እንዳልከው ግራ አጋቢ ሁኔታ ነው" የመረጃ መኮንኑ መልስ እየሰጠው አንዱን በተን ሲጫነው ቢጫ መብራት አብርቶ ጸጥ አለ።

አረንጓዴውን ሲጫነው ተመሳሳይ አረንጓዴ መብራት በራና የነበሩበት ወለል ሲነቃነቅ ተሰማቸው። አውሮፕላን ሲያርፍና ሲነሳ የሚያሰማው ንቅናቄ ዓይነት የሚፈጥረው ስሜት ነበር የተሰማቸው። ቀዩን ሲጫነው እንደ መንቃነቅ አለና ሁሉም ነገር ጸጥ ሲል የበራው መብራትም ቀስ እያለ ከሰመና ጠፋ። ቀዩን መልሶ ሲጫነው የአደጋ ምልክት ሰጠና መጮኽ ሲጀምር እንደ በፊቱ መነቃነቅ ጀመረ። ንቅናቄው ውስጡን የመረበሽ ስሜት ስለ ሰጠው መልሶ አጠፋውና ማሰብ ጀመረ። እንዲህ ዓይነት የድፍረት ቴክኒሻንነት በራሱ አደጋ ነው። በሳት እንደ መጫወት። ለራሱ በውስጡ ፈገግ አለ።

"እነዚህ ነገሮች ባለሙያ የሚስፈልጋቸው ይመስለኛል" የጸጥታ ፖሊሱ ሐሳብ ሰነዘረ።

"ለቴክኖሎጂ መሣሪያ የሚሆን የሠለጠነ ባለሙያ የለንም። እራሳችን ሙያውን መፍጠር ይኖርብናል።"

አረንጓዴውን ሲጫነው የቆሙበት ስፍራ ከፍተኛ ንቅናቄ ከአሰማ በኋላ የሞተር ዓይነት ድምጽ ተከተለ። ቀስ በቀስም የነበሩበት ቦታ ንቅናቄ እየጨመረ "ሲጢጥ" የሚል ድምጽ ከመሰማቱ የቆሙበት ወለል በአንድ ሜትር ያህል ስፋትና በሁለት ሜትር የጎን እርዝመት ከዋናው የቤቱ ወለል ተላቅቆ ቁልቁል መውረድ ጀመረ። እንቆቅልሹ ተፈታ ማለት ነው ተያዩ። በመረበሽ መካከል ፈገግታ እየተለጋገሱ ነበር። ደስታ ከፍርሃት ጋር...። እንቆቅልሹን ፈታሁት. . .። አንሾካሾከ መኮንኑ።

ዝቅ እያለ በወረደ መጠን ከውስጥ ወደ ላይ የብርሃን መስመር በሊፍቱ የመስታወት መስኮት መግባት ጀመረ። ግማሽ ሜትር እርቀት ላይ እየወረደ ነው። የመረጃ መኮንኑ በጭንቀት ከንፈሩን እንደ ነክሰ የጸጥታ ፖሊሱን አስተዋለው። ከታችኛው ክፍል ወደ ላይ እየመጣ ያለውን ኃይለኛ የብርሃን ጨረር ከዓይኑ ላይ ለመከላከል ሲሞክር በሸጉጡ ጫፍ የገዛ ግንባሩን ገጨው።

ወደ ጸጥታ ፖሊሱ ቀና ሲል

"ግንባርክን ምን ሆንክ? እየደማ ነው ሲል ጠየቀው ሊፍቱ ከፍተኛ ንቅናቄ አሰምቶ ሲቆም በሩ እንደ ተዘጋ ነበር ያለው። ለምን አልተከፈተም ሁለቱ ሰዎች ተያዩ።

በድቅድቅ ጥቁር ጨለማ የተዋጠው ስፍራ እንደ ሲኦል የሚያስጨንቅ ክብደት ነበረው። ከቅዝቃዜውም ደስ በማይል ጠረን የታመቀ ነው። እርጥበቱ በፈጠረው የአየር መታመቅ የሚያቅለሸልሽ ሽታ ተፈጥሯል። ከሰፊው ክፍል ውስጥ እንደ ቆሙ መጥፎውን ሽታ ለመከላከል አየር ላለመሳብ ቢታገሉም አልቻለም።

"የሚያስጠላ ሽታ አለው" አለ የመረጃ መኮንኑ።

"ከተቻለህ አየር ወደ ውስጥ አትሳብ"። የጸጥታ ፖሊሱ ታገለ።

"ሲኦል እንደዚህ የሚከብድ ከሆነ የሰው ልጅ ከፈጣሪው ሊያጣላው የሚችል ጥፋት መሥራት አልነበረበትም። የመረጃ መኮንኑ አጠገቡ የነበረውን የጸጥታ ፖሊስ ረስቶት በረጅሙ እያወራ ነበር።

"ምን አልከኝ" አለው ፖሊሱ።

"የተናገርኩት ለራሴ ነበር" የመረጃ መኮንኑ በጭንቀት ውስጥ ፈገግ አለ በሃፍረት።

የከበበውን ጥልቅና ግዙፍ ጨለማ እንደ ሰንጢ በመግመስ ግዝፈቱን እያጎላች የምታሳየው ትንሽ ባትሪ የመጥፎ ነገር ምልክ መሰለችው።

አጠፋትና ከጨለማው ጋር ትንሽ ለመለማመድ ሞከረ። የማይታሰብ አጉል ሙከራ ነበር። መልሶ አበራትና አጠገቡ የነበረውን የጸጥታ ፖሊስ በውጋገኑ አየው።

ከሩቅ የሚመጣ አንድ አይነት ድምጽ አለ። ድምጹ የምን እንደ ሆነ መለየት አይቻልም" አለው።

ወደዚያውም ድቅድቁ ጨለማ የሳሳ መሰለውና የክፍሉን ዙሪያ አንገቱን እያሿሿረ ፈተሸው። በርግጥ ድቅድቁ ጥቁር ጨለማ ቀስ በቀስ እየሳሳ ከላይ ወደ ታች ደብዛዛ ብርሃን እየመጣ ነበር። አሳንሰሩ ወደታች ለመምጣት ተንቀሳቅሷል።

"አሳንሰሩ እየመጣ ነው" የጸጥታ ፖሊሱ አንሾካሾከለት።

ባለመስታወቱ አሳንሰር እየመጣ ያለው አንድ ሰው ይዞ ነው። ሰውየውን ብቻውን እንደ ቆመ ተመለከቱትና ግራ ተጋቡ።

"ወደ ጥልቅ ገሃነመ ጨለማ እንደሚገባ አያውቅ ይሆን?" ሲሉ ሁለቱም አሰቡ። ከአሳንሰሩ ውስጥ የነበረው ሰው የውኃ ዋናተኞች ባትሪ ከግንባሩ ላይ አስሯል። በእጁ ላይ አውቶማቲክ ሽጉጥ እንደ ጨበጠ በጀርባው የሸራ ቦርሳ አዝሎ ሙሉ ቱታ ለብሷል፡

የማይታሰብ ነገር ከየት የመጡ ናቸው። ራሱን ጠየቀ በሊፍቱ የመጣው ሰው።

"እንዳትንቀሳቀስ ሽጉጥህን ወደ መሬት ጣልና ቁም" የመረጃ መኮንኑ ዓይኑ ላይ የተተከለውን የሰውየውን ባትሪ ተቋቁሞ አስጠነቀቀው።

በሠለጠነ ዲፕሎማሲያዊ ቅልጥፍና የተባለውን አደረገና ፊቱን አዙሮ ቀጥ ብሎ ቆመ ከሊፍቱ የወጣው ሰው።

"ተንበርከክ" አለው ሽጉጡን እየተቀበለው።

ጀርባውን ለነሱ ሰጥቶ ትእዛዝ አክባሪነቱን ለማረጋገጥ ሽጉጡን ለቀቀለት።

"የምትፈልገው ምንድነው?" የጸጥታ ፖሊሱ ጠየቀው።

"በዚህ ሕንጻ ውስጥ ያለሁ ሠራተኛ ነኝ። እናንተስ ከዚህ ምን እየሠራችሁ ናችሁ?" አለ ሰውየው።

"የእኛ ማንነት አይመለከትህ" አለው ዘሩባቤል።

"እሺ" አለ ሰውየው።

"በየት በኩል ነው የመውጫያ በሩ?" የመረጃ መኮንኑ ጠየቀው።

"ከአለንበት በስተ ሰሜን በኩል ነው" አለ ሰውየው።

የሱ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ግልጽ አልነበረም። "ሰሜን በየት በኩል ነው" ሲል ጠየቀ የመረጃ መኮንኑ።

"እስረኞቹ በአሉበት አቅጣጫ ነው።" አለና መለሰለት።

"እስረኞቹ በዚህ ግራውንድ ውስጥ ናቸውን?" በፊት እንደሚያውቅ ሁሉ ጠየቀው።

"አዎን ከዚህ ግራውንድ ውስጥ ነው ያሉት" አለው።

"ቅደም ከፊት ምራን" አለ የመረጃ መኮንኑ።

የመውጫያ በር ነው ከተባለው ስፍራ ሲደርሱ





"ይህ ነው መውጫያው?" ሲል ጠየቀው የመረጃ መኮንኑ።

"አዎን" አለው ሰውየው። በጨለማው ውስጥ በግንባሩ እየጠቆመው።

"ወደ እስረኞቹ ክፍል ምራኝ"። አለው የመረጃው መኮንኑ።

"እየሄድሁ ያለሁት ወደነሱ ነበር" አለ ምርኮኛው።

"ምን ልትሠራ ነው ወደነሱ የምትሄደው?"

"ልጉበኛቸው ነው።"

"በጣም ጥሩ" አለ የመረጃ መኮንኑ።

የሰውየው ባትሪ ለጨለማው ረድቷቸዋል።

በጥርብ ድንጋይ በተከፈለው ኮሪደር ለተወሰኑ ደቂቃዎች እንደ ሄዱ ኮሪደሩ ወደ ቀኝ ታጠፈና ከፊት ለፊታቸው በፌሮ ብረት ተማግረው የተሠሩ መጠነኛ ስፋት ያላቸው ክፍሎች መደዳውን ታዩአቸው። በክፍሎቹ ውስጥ የበራው መብራት የምድር ውስጥ ጽልመቱን ተቆጣጥሮት ዶቃ ያሳያል።

የመረጃ መኮንኑና የጸጥታ ፖሊሱ እርስ በእርስ ተያዩ። ኮሪደሩ ሦስት ሜትር ያህል የሚያሰፋ ሲሆን በሴራሚክስ የተነጠፈ ነው።

የእስረኞቹ ክፍሎች በሮቻቸው በትላልቅ የችንካር ቁልፎች ተቆልፈው በበሮቹም ላይ የጽሑፍ ታፔላ ተንጠልጥሎ ይታያል።

የፍርዳቸው ዘመንና ጥፋታቸውን የሚገልጽ ጽሑፍ በእስረኞቹ በር ላይ ተንጠልጥሏል።

"ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተፈረደበት።" የሚለውን አነበቡት "የሠራው ወንጀል የመንግሥት ሰላይ የነበረ ነው" ይላል። እያንዳንዱን እያነበቡ ሄደው ቁጥር አርባ ላይ ሲደርሱ የክፍሉ መጨረሻ ደረሱና ወደ ግራ ታጠፉ። በዚህ መስመር ያሉት እስረኞች አብዛኛዎቹ አፍሪካውያንና ቻይናውያን አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ነጮች ነበሩ። የእስረኞቹ ክፍል ቁጥር አንድ መቶ ላይ ሲደርስ ቆመ። የሚቀጥሉ ክፍሎች ቢኖሩም መብራት ያልበራባቸው በመሆናቸው እስረኛ እንደ ሌለባቸው ገመተ የመረጃ መኮንኑ።

"የዕድሜ ልክ እስረኛ ነህ?" የመረጃ መኮንኑ ከመጨረሻው ክፍል ያለውን እስረኛ ጠየቀው።

"የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተፈረደብኝ" አለ እስረኛው።

"ማነው ያሰረኽ? ጥፋትህስ ምን ነበር?" ሲል በተገርሞ ጠየቀው።

"የሥነ ምግባር ጉድለት ነው።" እስረኛው በጣም አዝኖ መለሰለት።

"የምን ሥነ ምግባር?" የመረጃ መኮንኑ በመገረም ተመለከተው።

"የምንሠራበትን ድርጅት በታማኝነት አላገለገላችሁም በሚል የሥነ ምግባር ጉድለት ፈጽማችኋል ተብለን የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተፈረደብን ነን አለ።

"ማነው የሚፈርድባችሁ?" አለ የመረጃ መኮንኑ።

"የጠረፉ ንጉሥ ጊዜያዊ ፍርድ ቤት ነው" አለ እስረኛው።

"ሁላችሁም ጥፋታችሁ አንድ ነው?" የመረጃ መኮንኑ ከሱ ቀጥሎ

ያለውን እስረኛ እየተመለከተ ጠየቀው::

"በዚሁ መደዳ የምንገኘው ተመሳሳይ ፍርደኞች ነን:: የሌሎቹን ወንጀል አላውቅም::"

እስረኛው እምባው መውረድ ስለ ጀመረ አሳዘነው::

"አትነጋገሩም እንዴ?" የመረጃ መኮንኑ ፊቱን መልሶ መደዳውን ያሉትን እስረኞች እየተመለከተ ጠየቀው::

"ስለምንራራቅ አንነጋገርም" እስረኛው በእንባ ውስጥ ተናገረ::

"የሌሎቹ ፍርድ ዕድሜ ልክ አይልም እኮ" አለ የመረጃ መኮንኑ::

"ተሻሽሎላቸው ነው::"

"ማነው ያሻሻለላቸው?"

"የጠረፉ ንጉሥ" እስረኛውን እልህ ሲተናነቀው ሳግ ይተናነቀው ጀመር::

የመረጃ መኮንኑ ስለ ጠረፉ ንጉሥ ማብራሪያ አገኛለሁ ብሎ ጓጓ:: "ማነው የጠረፉ ንጉሥ?"

"አላውቅም:: የጠረፉ ንጉሥ ብለው የሚነግሩን እነሱ ናቸው::"

"የሚያሠራችሁ ምንድን ነው?" የጸጥታ ፖሊሱ ያደምጣል::

"የማንሠራው ነገር የለም::"

"የጠረፉ ንጉሥ የት ነው የሚኖረው? አይተኸው ታውቃለህ?" አለው የኃሳቡን ንጉሥ በአእምሮው ምን እንደሚመስል እየሳለው::

"እሱን አይደለም ድርጅቱን እንኳን በውል አናውቀውም::"

"ዜግነትህ ምንድነው?" ሲል ጠየቀው::

"አልጄሪያዊ ነኝ::" አንገቱን በመጠኑ ዘንበል አደረገ::

"የሥራ ድርሻህ ምን ነበር?" የመረጃ መኮንኑ አተኩሮ ተመለከተው::

"የሜርኩሪ ውህድን ከእውነተኛ ሜርኩሪ ጋር እያመሳሰልሁ እሠራ ነበር::"

"ከአንተ ቀጥሎ ያለውስ ምን ይሠራ ነበር?" አለው::

"እራሱን መጠየቅ ትችላለህ::" ሲል መለሰለት::

"እንግሊዝኛ መናገር ይችላል እንዴ?" አለው የመረጃ መኮንኑ::

"በመጠኑ ስለሚችል ተግባብቷችሁ ትነጋገራላችሁ::"

የመረጃ መኮንኑ ፊቱን ሲመልስ በየክፍላቸው ቆመው ወደሱ አቅጣጫ ሲመለከቱ በዓይን ተገጣጠሙ::

ከሚቀጥለው ክፍል የነበረው እስረኛ ዓይኑን እያቁለጨለጨ ሲመለከተው አንድ ነገር ሊለው የፈለገ መሆኑ ገባውና ወደ በሩ ተጠጋ:: እንደ ዱር አራዊት መኖሪያ በፍርግርግ ክፍል የተቀየዱት እስረኞች ምን ያህል የሥነ ልቦና ቀውስ እንደሚደርስባቸው ማሰብ ቀላል ነበር::

እስረኛው እንደ ጦጣ ብልጣብልጥ ይመስላል:: ሰላምታ ሲሰጠው በቅልጥፍና ጎንበስ ብሎ እጅ ነሳቸውና ተቁነጠነጠ::





"ዜግነትህ ምንድነው?"

"ጀርመናዊ ነኝ:: ከኔ ቀጥሎ ያለው አሜሪካዊ ከሱ ቀጥሎ ያሉትም አንዱ ፈረንሳዊ አንዱ ደግሞ እንግሊዛዊ ከሱ ቀጥሎ ያለውም ሆላንዳዊ::" አንዱን በአንዱ ላይ እያነባበረ የነገረው ሳይጠየቅ ስለነበር አእምሮው ትክክል ያልመሆኑን ተረዳ የመረጃ መኮንኑ::

እራሱን ወደ ሴትነት እየለወጠ መሆኑን ሲረዳም ንዴት አገነፈለው:: እስረኛው ግን እንደ ቀጠለ ነው::

"ከስምንተኛው ክፍል ቀጥሎ ያሉት እስራኤላዊና ሞሮኮያዊ ናቸው::" ትንፋሽ እየወሰደ ያልተጠየቀውን ጭምር ይዘረዝርለት ጀመር:: ድምጹን ሳይቀር ወደ አንስታይ ፆታ ለመለወጥ እየሞከረ መሆኑ የበለጠ አበገነው::

"በምን ምክንያት ነው የታሰርከው" እንቅስቃሴው እያቅለሸለሸው ቢሆንም ታገሰ::

"ሥነ ምግባር አላከበራችሁም በሚል ነው::"

"አንድ ሰው የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈጸመ የሚባለው ምን ፈጽሞ ሲገኝ ነው::" የመረጃ መኮንኑ እየተገረመ ጠየቀው::

"የክፍያ ጥያቄ አንስቼ ነው እኔ የተፈረደብኝ::"

ለምን የክፍያ ጥያቄ አቀረባችሁ? ወንጀል መሆኑን ቀደም ሲል አላስረዷችሁም እንዴ?"

"ከአንድ ናይጄሪያዊ ላይ የተቀበልኩትን አልማዝ ነበር እንዲሰጠኝ የጠየቅሁት እሱን ይገባኛል ብዬ ጠይቄ ነው በዕድሜ ልክ እስራት የተቀጣሁት::"

"ሕጋችሁን የምታውቅ ከሆነ ለምን ጠየቅህ?" የመረጃ መኮንኑ ጥያቄውን በጥያቄ ደገመለት::

"ከሠራሁት አንድ ፐርሰንት ያህል ስለ ነበር የጠየቅሁት ያስቀጣኛል የሚል ስጋት አልነበረኝም::"

"የጠየቅኸው የገንዘብ ድርሻህ ከፍተኛ አልነበረም እያልከኝ ነው?" አለ የመረጃ መኮንኑ::

"ከሠራሁት ሲነጻጸር እጅግ ጥቂት ገንዘብ ነበር::"

"ከድርጅቱ ለመልቀቅ የፈለግኸው ለምን ነበር?"

"ኩላሊቴን ስለ ሰረቁኝ ጤና አይሰማኝም::"

"አልገባኝም" አለ የመረጃ መኮንኑ::

በቀኝ በኩል ቲሸርቱን ሽቅብ ሰብስቦ ሽንጡ ላይ የተገመሰውን ጠባሳ እያሳየው "ይኸውልህ ኦኘራሲዮን አድርገው ኩላሊቴን ወስደውታል" አለው::

እያንዳንዳቸው የተለያዩ የውስጥ አካላቸው እንደተመዘበረባቸው አልተጠራጠረም::

"የኬሚስትሪ መምህር ስለነበርሁ ውህዶቹን የማቀናብራቸው እራሴ ነበርሁ" እምባውን እያፈሰሰ መለፍለፉን ቀጠለ::

“መምህር ነበርክ ማለት ነው?” አለና ጠየቀው።

“መምህር ብቻ ሳልሆን ተመራማሪም ነበርሁ።”

“ከመምህርነቱ ዝርፊያው ተሻለህና ወደ ኢትዮጵያ ገባህ?” ሳቅ አለ በምፀት።

“ወደ ኢትዮጵያ የገባሁት ለምርምር ሥራ ነበር። በአጋጣሚ ከጠረፉ ንጉሥ ሠራተኞች ጋር ተገናኘሁ። ቀስ በቀስም ወደነሱ እየሳቡ አስገቡኝ። ተመልሼ መውጣት ለሕይወቴ አደጋ ስለ ነበር ለነሱ መሥራት ጀመርሁ።”

“የጠረፉ ንጉሥ ብለህ የምትጠራውን ሰው አይተኸው ታውቃለህ? የመረጃ መኮንኑ ትኩር ብሎ እየተመለከተው ስሜቱን አጠናው።

“በዓይናችን አናየውም። የማይታየው መንፈስ ስለሆነ ነው ይለናል።”

“መንፈስ ነው እያሉ በቁማችሁ እያታለሉ በለቷችሁ?”

“ያሰብነውንና የተመኘነውን ሁሉ የሚያውቅ መንፈስ ነው ብለው ስለነገሩን መፍራት ጀመርን። በቃ ይሄው ነው” አለው እያለቀሰ።

“የተማርህ ሆነህ ይህንን እንዴት አመንህ?” አለ የመረጃ መኮንኑ

“ለምን አላምንም? ከድርጅቱ ለመውጣት አስበው ብዙዎቹ ተገድለዋል እኮ!” ሲል ፍርሃት ባጀበው ቅላፄ መለሰለት።

“የተገደሉም አሉ ማለት ነው?” የመረጃ መኮንኑ ጠየቀው።

“ሰባተኛው ምድር ሲኦል ተብሎ የሚጠራው ክልል የነሱ የመቃብር ስፍራ ነው።”

“የተገደሉትን ታውቃቸዋለህ?” የመረጃ መኮንኑን ቀልብ የሳበ ጥቆማ ነበር የተናገረው።

“በስም አውቀዋለሁ ካለንበት ቀጥሎ ይመስለኛል ያለው።”

“በምንድነው የሚገድሏቸው?”

“የውስጥ ዕቃቸው እየተመዘበረ ሲወሰዱ ይሞታሉ።”

“ገባኝ” አለ የመረጃ መኮንኑ” የውስጥ ዕቃቸውን አውጥተው ሲጨርሱ ይሞታሉ። የቅጣተኝነት “ፍርድ የሚሰጡት አካላት የትነው ያሉት?”

“መጨረሻው ፎቅ ላይ ይመስለኛል የሚኖሩት።” እስረኛው መለሰ።

“የጠረፉ ንጉሥ የተባለው ሰው ምን ይመስላል?” አሳማውን ሰው በልቡ እያሰበ ጠየቀው። ያ የተረገመ ድቡልቡል·መሆን አለበት አለ ለራሱ።

“በጣም የሚያስጠላ ውፍረት ያለው ሰው ነው” ሲል መለሰለት።

“እሱን እኮ ይዤዋለሁ።” አለ መኮንኑ።

“ይዘኸዋል እንዴ?” ደንገጥ ብሎ ተመለከተው።

“ከሴቶች ጋር ሲሰስን ነው የያዝኩት። በኔ ቁጥጥር ስር ሆኗል።”

“እንዴት ያዝከው? መንፈስ ነኝ ይል ነበር እኮ።”

“እንኳን መንፈስ ጉንፋን የለበትም” አለው ሳቅ ብሎ።

“የጠረፉ ንጉሥ በኔ ላይ ሆኖ ሁሉንም ያደርጋል እያለ አታለለን።”

“ያታለላችሁ የራሳችሁ ደደብነት ነው።”





“ወሲብ ሲሠራ ሁለቱ ራቁታቸውን በመሆን ከፊት ለፊቱ የሚቆሙ ሴቶች አሉ። ከፊት ለፊቱ ቆመው በልዩ እንቅስቃሴ በወሲባዊ ምትሃት እራቁት ሰውነታቸውን ሲያሳዩት ሦስተኛዋ ከላዩ ላይ ሆና ትጨፍርበታለች። እንደረካም ሌሎች ወንዶች ወደ ክፍሉ ይገቡና ከኮረዳዎቹ ጋር ወሲብ ይፈጽማሉ።”

“ወሲብ በሚፈጽምበት ወቅት ወደሱ ትቀርብ ነበር ማለት ነው?” የመረጃ መኮንኑ ትክ ብሎ ተመለከተው።

“ይፈቀድልን ስለነበር እኔም ደርሶኛል” እስረኛው ስሜት ውስጥ እየጠለቀ ደረትና ሆዱን አሻሸ።

“አንተም ድርሻህን ፈጽመሃል ማለት ነው?” የመረጃ መኮንኑ ኮስተር አለ።

“ፈጽሜያለሁ። እንዴት ያለ ድንቅ ጨዋታ ነበር መሰለህ። የሴቶቹን ወሲባዊ ስልት ስትመለከት ቆይተህ ስትፈጽመው እንዴት ያለ ደስታ ይሰጣል መሰለህ” ዓይኖቹን ከደነ።

“ሴቶቹ ከየት ነው የሚመጡት?” የመረጃ መኮንኑ ጠየቀው።

“በደላላ አማካይነት ይመጣሉ” ዓይኑን ከድኖ ስሜቱን እያዳመጠ መለሰለት።

“አልገባኝም” የመረጃ መኮንኑ ትክ ብሎ አስተዋለው።

“የሚመጡት ወጣቶች የሚቆዩት ለሦስት ቀን ብቻ ስለሆነ በየጊዜው ይቀያየራሉ።”

አዲሶቹ ሲገቡ የበፊቶቹ ወዴት ይሄዳሉ?”

“ምናልባት አካላቸው ይወጣና ይጣሉ ይሆናል” የሚል ነው ግምቱ።

“ለመለዋወጫህ አንተም ተራ እየተጠበቀልህ ይሆን?” ሲል ጠየቀው መልስ ሳይሰጠው በራሴ ስሜት ገብቶ መለፍለፍ ጀመረ።

“ለሰው ልጆች ከተሰጡት ድንቅ ነገሮች አንዱ ወሲብ መሆኑን ታምናለህ? ወሲብ ባይኖር ኖሮ ሕይወት እንዴት ባስጠላች ነበር።”

“አንተ ውሻ የምጠይቅህን መልስ።” ከዚያ በኋላ ሊሰማው አልቻለም።

አራተኛ ፎቅ ላይ ጠፍሮ ያሰረው ወፍራም ሰው ትዝ ሲለው የመረጃ መኮንኑ በአሸናፊነት ልቡ በእፎይታ ስትተነፍስ ታወቀው። ያ ድቡልቡል ሰው የጠረፉ ንጉሥ ነኝ ብሎ እራሱን ሰይሟል ማለት ነው። የውሻ ልጅ እያንዳንዱን አካሉን እየነቃቀልሁ እጫወትበታለሁ ሲል በውስጡ ከፋኛ ዛተበት።

“የተረገማችሁ ፍጥረቶች ናችሁ” በቁጣ ጮኸበት።

ከሚቀጥለው ክፍል ሽርጥ መሳይ ያጠለቀው ወፍራም ሰው ድምጹን እንደ ሴት አቅጥኖ አንድ ነገር ተናገረና መቅለስለስና መሽኮርመም ጀመረ። “የውሻ ልጆች።”

ጀርመናዊው እስረኛ ሽርጡን ከፍ ከፍ እያደረገ ስለነበር ሌላ ነገር

ከማየቱ በፊት ድርጊቱን ማስቆም *እንዳለበት ተገነዘበ። ከጭንቅላቱ ከፍ አድርጎ ሲተኩስ በድንጋጤ በድን ሆነና ከወለሉ ላይ ወደቀ።

"አንተ የማትረባ? የእናንተ ሥልጣኔ ይኼ ነው። ልክስክሶች አገራችንን ያጠፋችሁ ወንጀለኞች ስለሆናችሁ ሁላችሁንም እፈጃችኋለሁ። በጥያፌ ተመልክቶት ወደ መጡበት አቅጣጫ ሲራመድ የጸጥታ ፖሊሱ በሁኔታው ተገረመ።

"በዚህ ሁኔታ ካሉ ሰዎች ምን ትጠብቃለህ" አለው።

ጥይት የፈነዳባቸው እስረኞች በብረቱ ፍርግርግ አጮልቀው እየታዩ የእንኳን አተረፈህ እና አተረፈሽ የስስት ሰላምታ ቃላት በዓይን እየተጠቃቀሱ ሲጠያየቁ ሲመለከት ራሱን አስጠላው።

አንዳንድ እስረኞችም በየመኝታዎቻቸው ላይ ወዳድቀው አንገታቸውን ደፍተው አይንቀሳቀሱም ነበር።

ከነሕይወታቸው ተቀብረው ሞትን ሲፈሩ ሲመለከት እጅግ አድርጐ ገረመው።

"ለምንድነው ያደፈጣችሁት" የጸጥታ ፖሊሱ አንደኛውን ጠየቀው።

"ለምን ትገድሏችኋላችሁ?" እንደ ተማከሩ ሁሉ ተመሳሳይ ጥያቄ በአንድ ላይ አቀረቡ ።

"መሞት ያለባችሁ ቆሻሻና መጥፎ ሰዎች ናችሁ።" አለ የመረጃ መኮንኑ።

"ትገድለናለህ ማለት ነው?" ቻይናዊ የተጨፈኑ ዓይኖቹን እየገለጠ ጠየቀው።

ድምጹ የቀጠነና የሰውነት እንቅስቃሴያቸውም የሴት አይነት ስለነበር የተረገምህ ቡችላ አለ በልቡ የመረጃ መኮንኑ።

ከሚቀጥለው ክፍል የነበረው አሳዛኝ ፍጥረት መለፍለፍ ጀመረ።

"ግብረሰዶማውያን ናችሁ አይደል?" የመረጃ መኮንኑ በሚያስገመግም ቃል ጠየቀው።

ድምጹ ብቻ አይደለም የተቀየረው የሰውነት እንቅስቃሴውም የተለየ ነበር። በልዩ ስልት ይሽኮረመማል። ሴት ወንድ ሴት ወንድ ተባብለው በመሰያየም የወደቁና የረከሱ ፍጥረቶች ሆነዋል። እነዚህ ርጉሞች ቅጣታቸውን እያገኙ ናቸው። የመረጃ መኮንኑ ወደ ቻይናዊው እስረኛ ተመለከተ። ወፍራም የዓይን ቆቦቹ ዓይኖቹን ስለዘጉበት ለመግለጥ ከአንገቱ ጭምር ቀና በማለት ላይ ነበር።

"አንተ የተረገምህ ምርግ" አለ የጸጥታ ፖሊሱ።

"እዚሁ እንዳለህ እገድልሃለሁ።"

አንገቱን አቅለሰለሰና የዶቃ ብስ ዓይኖቹን በሀይል ለመግለጥ ሽፋሉን የበለጠ ሽቅብ ሰበሰበ።

"ከዚሁ እንጨርሳችኋለን" በእንግሊዘኛ ቢናገርም የሚለው





እንዳልገባው ስለገባው ዳሩ የታባክ የተማርከውን? ብሎት ፊቱን መለሰ።

የመረጃ መኮንኑ እራሱን በቁጭት ነቀነቀ። "እነዚህ ውሾች ሀብትና ቅርሳችንን ብቻ አይደለም የዘረፉን። ባህልና እምነታችንንም ጭምር አውድመውታል። ለዚህ ጥፋታቸው በተቀበሩበት በስብሰው እንዲያልቁ አደርጋቸዋለሁ።"

የጸጥታ ፖሊሱ ወደ ኢትዮጵያኑ እየተመለከተ "የኛዎቹም ተበክለዋል እያልከኝ ነው?" ሲል ጠየቀው የመረጃ መኮንኑን።

"ከነዚህ ውሻዎች የተለየ ነገር ይኖራቸዋል ብዬ አላምንም" አለ የመረጃ መኮንኑ። ከመውጫው በመጨረሻው ክፍል የነበረው እስረኛ ሰው የተሰወረው የጸጥታ ሠራተኛን ይመስላል።" አለ ለራሱ እርግጠኛ ነው። ይህ ሰው ራሱ የደረሰበት የጠፋው የጸጥታ ሠራተኛ ነው።

እርግጠኛ ለመሆኑ ራሱን በራሱ ማሳመን ነበረበት። በተደበላለቀ ስሜት እንደተዋጠ ፊቱን ወደ ጸጥታ ፖሊሱ መለሰ። እሱም ግራ በመጋባት ወደ እስረኛው አቅጣጫ እየተመለከተ ነበር። ሁኔታው ግራ አጋቢ ነው። የት እንደደረሰ ሳይታወቅ ተሰውሮ የነበረው የሀገር ውስጥ የደኅንነት ሠራተኛ እዚህ ታስሯል። ከፖሊሱ ጋር በድጋሚ እርስ በርስ ተያዩ።

"ይህ ሰው ማን እንደ ሆነ ታውቃለህ?" ጠየቀው የመረጃ መኮንኑ።

እራሱን በአወንታ ነቀነቀ "ይመስለኛል። እንዲያውም እርግጠኛ በመሆን መናገር እችላለሁ።"

"የሀገር ውስጥ የደኅንነት ባልደረባ ነበር" የመረጃ መኮንኑ ተናገረ።

"ትክክል ነህ። ሲቪል ደኅንነት ሆኖ የመረጃ ሥራ ይሠራ ነበር።" የጸጥታ ፖሊሱ አረጋገጠለት።

የመረጃ መኮንኑ ፊቱን ወደ እስረኛው መልሶ በድጋሚ ተመለከተ። እስረኛውም በተራው የመረጃ መኮንኑን በጥልቀት አስተዋለው።

"ከዚህ ምን አምጥቶ ጨመረሽ?" የመረጃ መኮንኑ በአግራሞት እየተመለከተ ጠየቀው።

"በሥራ ላይ እንዳለሁ በቡድኑ የደኅንነት ሠራተኞች ተጠልፌ ነው።" አለ እስረኛው የሀገር ውስጥ የደኅንነት ባልደረባ።

"ከአንተ ጋር የተያዙ ሌሎች እስረኞች አሉ?" የመረጃ መኮንኑ ጥያቄ የግራ መጋባት ይመስላል።

"እኔ ብቻ ነኝ ያለሁት። አንደኛውን እንደተያዝን ነው የገደሉት" እምባ ስለተናነቀው አንገቱን አቀረቀረ።

ያለ ጥርጥር ብዙ ስቃይ ደርሶበታል ማለት ነው ሲል አሰበ የጸጥታ ፖሊሱ።

"አንተንስ እንዴት አልገደሉህም?" የመረጃ መኮንኑ በመገረም እየተመለከተ ጠየቀው።

"እኔም የገረመኝ ይኼው ነበር።" በረጅሙ ተነፈሰ እስረኛው።